# በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር
# የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን

## የ1997 ዕቅድ አፈጻጸም
## ግምገማ ሪፖርት

አዲስ አበባ
ሐምሌ 1997

# በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር

# የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን

## የ1997 ዕቅድ አፈጻጸም

## ግምገማ ሪፖርት

አዲስ አበባ

ሐምሌ 1997

# ማውጫ


ርዕስ ገጽ

1. መግቢያ ........................................................................................ 1
2. የኢኮኖሚክ ስታቲስቲክስ ........................................................................ 3
   2.1 የተፈጥሮ ሃብትና ግብርና ስታቲስቲክስ ጥናት ...................................... 3
   2.2 የቤተሰብ በጀትና ዋጋዎች ስታቲስቲክስ ጥናት ...................................... 6
   2.3 የኢንዱስትሪ፣ንግድ፣ ትራንስፖርትና መገናኛ ስታቲስቲክስ ጥናት ....... 10
   2.4 የማህበራዊ ስታቲስቲክስ ጥናት ......................................................... 12
3. 1997 በጀት ዓመት የፊዚካል ሥራ አፈጻጸም ............................................ 16
4. ሳምፕሊኒንግ ሜቶዶሎጂን በተመለከተ .................................................... 17
5. የአካባቢ. ጽ/ቤቶችና የመስክ ሥራ ክንውን ተግባራትን በተመለከተ .............. 21
6. የመረጃ ማቀነባበርን በተመለከተ ........................................................... 22
7. የኢንፎርሜሽንኮሙኒኬሽን ...................................................................... 25
8. የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ጽ/ቤት ዝግጅትን በተመለከተ ............................... 28
9. የማስታወቂያና ሕዝብ ግንኙነት አገልግሎት ............................................... 31
10. የኦዲት አገልግሎት ................................................................................ 33
11. የሕግ አገልግሎት .................................................................................. 34
12. የፕላንና ፕሮግራም አገልግሎት ............................................................... 35
13. የአስተዳደርና ፋይናንስ አገልግሎት .......................................................... 35
    13.1 የሰው ኃይል ሁኔታ ........................................................................ 35
    13.2 የበጀት አጠቃቀም .......................................................................... 37
    13.3 አገልግሎት ነክ የሆኑ ጉዳዮች ........................................................... 39
14. ኤች.አይ.ቪ/ ኤድስን በተመለከተ ............................................................. 42
15. በዕቅድ አፈጻጸም ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች .................................................. 43

## የ1997 በጀት ዓመት

## የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ ሪፖርት

### 1. መግቢያ

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን የተቋቋመበትን ዓላማና ግብ ለማሣካት ከመንግሥትና ከረጂ ድርጅቶች ከሚያገኘው የገንዘብና የሎጂስቲክስ ድጋፍ በየዓመቱ ለመረጃ ተጠቃሚዎች ጠቃሚ የሚሆኑ የተለያዩ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታዎችን የሚዳስሱ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን በመሰብሰብና በማቀነባበር የጥናት ሪፖርት በማዘጋጀት ያቀርባል፡፡ ይህንንም ለማሣካት በመላው አገሪቱ ገጠርና ከተማ በናሙና በተመረጡ የቆጠራ ቦታዎች የሠለጠኑ የመስክ ሠራተኞችንና ባለሙያዎችን በማሰማራት ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን ወቅቱንና ጥራቱን በጠበቀ መልኩ ይሰበስባል፡፡

በ1997 በጀት ዓመትም የባለሥልጣን መ/ቤቱ የመንግሥትና የሌሎች መረጃ ተጠቃሚዎችን ፍላጐት ያሟላሉ ያላቸውን እንዲሁም በየሴክተሩ ያለውን የመረጃ ክፍተት የሚያጠቡና ባጠቃላይ የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታዎችን የሚዳስሱ ጥናቶችን ለማካሄድ ዕቅድ በመያዝ በርካታ ተግባራትን አከናውኗል፡፡

በዚህም መሰረት የመረጃ ማሰባሰቡ ተግባር በ1996 ዓ.ም ተጀምሮ የመረጃ ማቀነባበሩ ተግባር ወደ 1997 የተሸጋገሩ የበልግ ወቅት የግብርና ናሙና ጥናት፣ የሰፋፊና መካከለኛ የግልና የመንግስት እርሻዎች ጥናት፣ የ1995 በጀት ዓመትን የሚመለከት የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንድስትሪ ጥናት፣ የኢኮኖሚያዊ ድርጅቶች አጠቃላይ ቆጠራ፣ የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ደህንነት ጥናት፣ የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት፣ ተከታታይ የሥራ ስምሪት ጥናት (ሁለተኛ ዙር) ቀሪ ሥራዎችን እንዲሁም ሌሎች አዳዲስ ጥናቶችን በዕቅድ በመያዝ ሰፊ የሥራ እንቅስቃሴ አድርጓል፡፡ በበጀት ዓመቱ የተከናወኑት ጥናቶችም የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ. የተፈጥሮ ሃብትና የግብርና ስታቲስቲክስ

- የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት
- የሰብል ምርት ጥናት በመኸር ወቅት
- የግል፣ የመንግሥትና የድርጅት የንግድ እርሻዎች ጥናት
- የሰብል ምርት ጥናት በበልግ ወቅት
- የቤት እንስሳት፣ የዶሮ ኃብትና ንብ የያዙ ቀፎዎች ጥናት

- የቋሚ ሰብሎች አትክልትና ሥራ ሥር ተክሎች ምርታማነት ጥናት

ለ. የኢንዱስትሪ፣ ንግድና ትራንስፖርት ስታቲስቲክስ

- የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት /በከተማ/
- ወቅታዊ የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት በሩብ ዓመት /በከተማ/
- የተፈበረኩ ዕቃዎች የምርት መጠንና የአምራቾች ዋጋ ጥናት በየሩብ ዓመት /በከተማ/
- የንግድና የአልግሎት ድርጅቶች ጥናት በየስድስት ወራት /በከተማ/
- የኢኮኖሚያዊ ድርጅቶችን ዝርዝር ወቅታዊ ማድረግ
- የውጪ ንግድ ስታቲስቲክስ መረጃ ማሰባሰብና ማጠናቀር
- የትራንስፖርትና መገናኛ መረጃ ማሰባሰብና ማጠናቀር

ሐ. የቤተሰብ በጀትና የዋጋዎች ስታቲስቲክስ

- የግብርና ምርቶች የአምራቾች ዋጋ ጥናት /በገጠር/
- የዕቃዎችና የአገልግሎቶች የችርቻሮ ዋጋ ጥናት /በከተማ/
- የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክሶች ዝግጅት
- የቤተሰብ ገቢ ፍጆታና ወጪ ጥናት (2ኛ ዙር)

መ. የማኅበራዊ ስታቲስቲክስ

- የሰው ኃይል ጥናት /በገጠርና ከተማ/ ናቸው።

በመሆኑም በበጀት ዓመቱ ውስጥ ከላይ የተዘረዘሩትን ሥራዎች አስመልክቶ የተከናወኑ ሥራዎችን ከዚህም ጋር የመ/ቤቱን የሰው ኃይል ሁኔታ፣ የበጀት አጠቃቀምና ሌሎች ተግባራትን የሚያሣዩ የጽሑፍና አሃዛዊ መረጃዎችን በዚህ ሪፖርት ውስጥ ለማቅረብ የተሞከረ ሲሆን፣ በተጨማሪም በዕቅድ አፈጻጸም ሂደት ያጋጠሙ ችግሮችና የበላይ አካል ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን አካቶ ቀርቧል።

## 2. የኢኮኖሚ ስታቲስቲክስ

### 2.1 የተፈጥሮ ሃብትና የግብርና ስታቲስቲክስ ጥናት

#### 2.1.1 የሰብል ትንበያ ጥናትን በተመለከተ

- የ1997 ዓ.ም የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት መረጃ የተሰበሰበባቸው መጠይቆች ዋናው መ/ቤት ደርሰው ለኤዲቲንግና ቬሪፊኬሽን ሠራተኞች ስልጠና በመስጠት የኤርማትና የቬሪፊኬሽን ሥራ ተጠናቋል። እንዲሁም ጥናቱን በተመለከተ መረጃዎቹን የማቀናበር ሥራ ተጠናቆና የትንተና ሥራ ተከናውኖ ሪፖርቱ ተዘጋጅቷል።

- የ1997 ዓ.ም የቅድመ ማስጠንቀቂያ የሰብል ግምገማ ጥናትን በተመለከተ በሃገሪቱ ከሚገኙ አብዛኛው የወረዳ ግብርና ጽ/ቤቶች የተሰበሰቡ መረጃዎች ዋናው መ/ቤት ደርሰውና፣ በመምሪያው ባለሙያዎች የኤዲቲንግ፣ ኮዲንግና መረጃዎቹን ወደ ኮምፒውተር የማስገባቱ እንዲሁም የመረጃ ማቀነባበሩ ሥራና ሪፖርቱ ተጠናቋል።

- ለሁለተኛ ጊዜ ከወረዳ ግብርና ቢሮዎች የተሰበሰቡና ለ1997 ዓ.ም ቅድመ ማስጠንቀቂያ ትንበያ ሥራ የሚያገለግሉ መረጃዎችን ከመስከ እንዲሰባሰቡ በማድረግና አስፈላጊውን የቅንብር ሥራ በማካሄድ ውጤቱ ተዘጋጅቷል።

- የ1997 ዓ.ም መደበኛ የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት ድጋሚ በተካሄደባቸው 600 ቆጠራ ቦታዎች ጥናቱን እንደገና እንዲካሄድ በማድረግ መረጃዎች ተሰብስበውና ተቀነባብረው ውጤቱ ተዘጋጅቷል።

#### 2.1.2 የእርሻ መሬት ስፋትና የምርት መጠን መረጃን በተመለከተ

- በመስክ ደረጃ የመረጃ ማሰባሰቡ ተግባር የተጠናቀቀለት የ1996 የሰፋፊና መካከለኛ እርሻዎች ጥናት መረጃው የተጠናቀረ ሲሆን፣ የ1996 ዓ.ም የበልግ ወቅት ጥናት የእርሻ መሬት ስፋትና ምርት መጠን የመረጃ ቅንብር፣ የሪፖርት ዝግጅትና የሕትመት ሥራው ተጠናቆ ለመረጃ ተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል።

- የ1997 ዓ.ም መኸር ወቅት በሰብል የተያዘ መሬት ስፋትና ምርት መጠን ጥናት መረጃ ቅንብሩ ሥራ ተጠናቆና ሪፖርቱ ታትሞ ለተጠቃሚዎች እንዲሰራጭ ተደርጓል።

- ከጥቅምት ወር 1997 ዓ.ም ጀምሮ የመረጃ ማሰባሰቡ ተግባር ሲካሄድ የነበረው የአትክልት፣ ሥራሥር ተክሎችና ቋሚ ሰብል ጥናት የመረጃ ማሰባሰቡ ተግባር ተጠናቆ መረጃ የያዙ ቅጾች ወደ ዋናው መ/ቤት በመመለስ ላይ ይገኛሉ።

- የ1997 ዓ.ም የበልግ ወቅት ጥናት የመረጃ ማሰባሰቡ ሥራ በመስክ ደረጃ ተጠናቆ የኤዲቲንግና ኮዲንግ ሥራው ተከናውኖ መረጃውን ወደ ኮምፒውተር የማስገባት ሥራ በመካሄድ ላይ ይገኛል።

### 2.1.3 የመሬት አጠቃቀም

- የ1996 ዓ.ም መኸር ወቅት የመሬት አጠቃቀም መረጃ ቅንብሩ ተጠናቆና ሪፖርቱ ተዘጋጅቶ ለተጠቃሚዎች እንዲሰራጭ ተደርጓል።

- የ1997 ዓ.ም መኸር ወቅት መሬት አጠቃቀም መረጃ የኤዲቲንግ ኮዲንግና የኢንትሪ ሥራ ተከናውኖ መረጃው በኮምፒውተር ተቀነባብሮ ለህትመት በሚሆን መልኩ ተዘጋጅቷል።

### 2.1.4 የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታን በተመለከተ (Farm Management Practices)

- በ1996 ዓ.ም ከመስክ የመረጃ ማሰባሰቡ ተግባር የተጠናቀቀለት የሰፋፊና መካከለኛ እርሻዎች አጠቃላይ ሁኔታ የቅንብሩ ሥራ ተጠናቆ ሪፖርቱ ለህትመት በሚሆን መልኩ ተዘጋጅቷል።

- የ1996 ዓ.ም የበልግ ወቅት ጥናት የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ መረጃ የቅንብሩ ሥራና የሪፖርት ዝግጅቱ ተጠናቆና ታትሞ ለመረጃ ተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል።

- የ1996 ዓ.ም መኸር ወቅት የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ መረጃ ቅንብር ሥራና ሪፖርቱ ተዘጋጅቶ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል።

- የ1997 ዓ.ም መኸር ወቅት የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ መረጃ በኮምፒውተር ተቀነባብሮና የሪፖርት ዝግጅት ተጠናቆ ለህትመት ክፍል ተሰጥቷል።

2.1.5 <u>የቤት እንስሳት፣ የዶሮ ሃብትና ንብ የያዙ ቀፎዎችን መረጃ በተመለከተ</u>

- የ1997 የቤት እንስሳት የዶሮ ሃብትና ንብ የያዙ ቀፎዎችን ጥናት በተመለከተ ለመረጃ ቅንብር የሚያስችል የኤዲቲንግና ኮዲንግ መመሪያና ለ1997 ዓ.ም ለተካተቱት አዳዲስ መረጃዎች የመረጃ ማውጫ ሠንጠረዥ (Tabulation Plan) እንዲሁም የኮምፒውተር ስፔስፊኬሽን ዝግጅት ሥራ ተጠናቆ ሥራ ላይ ውሏል።

- የ1997 ዓ.ም የቤት እንስሳት ጥናት መረጃ የኤዲቲንግና ኮዲንግ ሥራ ተጠናቆ መረጃ ወደ ኮምፒውተር የማስገባት ሥራ፣ የመረጃ ቅንብርና ሪፖርት ዝግጅት ሥራው ተጠናቆና ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል።

2.1.6 <u>ሌሎች የተከናወኑ ተግባራት</u>

- ለ1997 ዓ.ም የቅድመ ማስጠንቀቂያ የሰብል ምርት ግምገማ፣ ለዋናው ሰብል ምርት ትንበያ፣ ለዋናው መኸር ግብርና ናሙና ጥናት፣ ለቤት እንስሳት ጥናት ለበልግ ወቅትና ለቋሚ ሰብል፣ አትክልትና ሥራ ሥር ተክሎች ጥናት እንዲሁም ለሰፋፊና መካከለኛ ንግድ እርሻዎች ጥናት የሚያገለግሉ የመረጃ አሰባሰብ መመሪያዎችና መጠይቆች ተዘጋጅተው በሥራ ላይ ውለዋል።

- የሰብል ምርት ትንበያንና የዋናው መኸር ጥናቶችን በተመለከተ በመስክ ደረጃ የዕርማትና የኮድ መስጠት ስራን ለማከናወን የሚያስችል መመሪያ ተዘጋጅቶ በስራ ላይ እንዲውል ተደርጓል።

- በ1997 በሠፈራ መንደር ለሚካሄደው የግብርና ጥናት መመሪያና መጠይቅ በማዘጋጀትና በማሠራጨት የመረጃ ማሰባሰቡ ተግባር ተጠናቆ የመረጃ ማቀነባበሩ ሥራ የተጠናቀቀ ቢሆንም በተለያዩ ምክንያት ስታቲስቲካል ሪፖርቱ አልወጣም።

- በ1994 የተካሄደውን የኢትዮጵያ ግብርና ናሙና ቆጠራ መረጃን በመጠቀም የሚመለከታቸው ባለሙያዎች በተለያዩ ግብርና ነክ ርዕሶች ላይ ጥልቅ የትንተና ሥራ (In depth analysis) በመሥራት የሀገር ውስጥና ዓለም አቀፍ የመረጃ ተጠቃሚዎች በተገኙበት በጥናቱ ውጤት ላይ የአንድ ቀን አውደ ጥናት ተካሄዷል፡፡

- ለሠፋፊና መካከለኛ እርሻዎች ጥናት የሚውል መጠይቅና መመሪያ ተዘጋጅቶ ለየቅ/ጽ/ቤቶቹ እንዲሰራጭ ተደርጓል፡፡

- መምሪያውን የሚመለከቱ ለዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት የሚውሉ መረጃዎችና የሌሎች መ/ቤቶች መረጃ በማሰባሰብ መረጃዎችን የማጠናቀር ሥራ ተከናውኖ ለሚመለከተው ክፍል ተሰጥቷል፡፡

- ከተለያዩ መ/ቤቶችና ድርጅቶች ለሚቀርቡ የመረጃ ጥያቄዎች ተገቢው ምላሽ ተሰጥቷል፡፡

- ለወረዳ ኔት ፕሮጀክት የሚያገለግሉ በወረዳ ደረጃ ሊሰባሰቡ የሚችሉ የመረጃ ዓይነቶችን አዘጋጅቶ ለሚመለከተው ክፍል ተላልፏል፡፡

- ለ1998 በጀት ዓመት ለሚከናወኑ የግብርና ናሙና ጥናቶች የሚውሉ መጠይቆች ላይ የዝግጅት ሥራዎች በመከናወን ላይ ይገኛሉ፡፡

## 2.2 የቤተሰብ በጀትና የዋጋዎች ስታቲስቲክስ ጥናት

### 2.2.1 የዋጋዎች ጥናትና የዋጋ ኢንዴክስን በተመለከተ

#### ሀ. በገጠር የግብርና ውጤቶች የአምራቾች ዋጋ ጥናት

- ስለመረጃ አሰባሰብና ቅጽ አሞላል መመሪያ ተዘጋጅቶ ለመረጃ ሰብሳቢዎችና ለመስክ ተቆጣጣሪዎች ሥልጠና የተሰጠ ሲሆን፤ ለ1997 ዓ.ም የሚያገለግል የአንድ ዓመት የመረጃ ማሰባሰቢያ ቅጽ ተዘጋጅቶ ለስታቲስቲክስ ቅ/ጽ/ቤቶች ተሠራጭቷል፡፡

- ከሐምሌ ወር 1996 ዓ.ም እስከ መጋቢት ወር 1997 ዓ.ም ድረስ ያለው የአምራቾች ዋጋ ጥናት ሪፖርት ተጠናቆና ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል።

- የሚያዝያ ወር 1997 ዓ.ም መረጃ ተቀነባብሮ ለህትመት የተላከ ሲሆን፣ የግንቦት ወር በመቀነባበር ላይ ይገኛል።

- በየሶስት ወሩ አንድ ጊዜ አንድ መጽሔት ይዘጋጅ የነበረው የአምራቾች ዋጋ ጥናት ሪፖርት የመረጃ ተጠቃሚዎችን ፍላጐት ለማርካት ሲባል በየወሩ እንዲዘጋጅ ተደርጓል።

ለ. <u>ወርሐዊ የዕቃዎችና የአገልግሎቶች የችርቻሮ ዋጋ ጥናት</u>

- ከሐምሌ 1996 ዓ.ም እስከ ሚያዝያ ወር 1997 ዓ.ም ድረስ ያለው ሪፖርት ታትሞ ለተጠቃሚዎች የተሠራጨ ሲሆን፣ የ1997 የግንቦት ወር መረጃም ተቀነባብሮ ለህትመት ተልኳል። የሰኔ ወር 1997 መረጃም በመቀነባበር ላይ ይገኛል።

- የመረጃ አሰባሰብ መመሪያ ተዘጋጅቶ ለመረጃ ሰብሳቢዎች ተቆጣጣሪዎች ሥልጠና ተሰጥቷል። እንዲሁም ለ1997 መረጃ ለማሰባሰብ የሚያስችል የአንድ ዓመት መጠይቅ ተዘጋጅቶ ለየቅ/ጽ/ቤቶች ተሠራጭቷል።

ሐ. <u>ወርሃዊ የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ጠቋሚ አሃዝ</u>

- <u>የሃገር አቀፍና የክልሎች</u>

  - የሀገር አቀፍና የክልሎች የሸማች ዋጋ መመዘኛ ጠቋሚ አሃዝ እስከ ግንቦት ወር 1997 ዓ.ም ያለው መረጃ በየወሩ ታትሞ ለተጠቃሚዎች እንዲደርስ ተደርጓል።
  - የሰኔ ወር 1997 ዓ.ም ጠቋሚ አሃዝ በመቀነባበር ላይ ይገኛል።

- <u>የአዲስ አበባ ከተማ</u>

  - የአዲስ አበባ ከተማ የሸማቾች ዋጋ መመዘኛ ጠቋሚ አሃዝ እስከ ሰኔ 1997 ዓ.ም ያለው መረጃ በየወሩ እየተቀነባበረና እየታተመ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል።

### 2.2.2 <u>የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናትን በተመለከተ</u>

- የ1996/97 በጀት ዓመት የመረጃ ማሰባሰቡ ተግባር ለተጠናቀቀለት የመጀመሪያ ዙር የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት ለኤዲቲንግና ኮዲንግ የሚያገለግል ዶኩመንት ተዘጋጅቶ በሥራ ላይ እንዲውል የተደረገ ሲሆን፤ በኤዲቲንግና ኮዲንግ ለሚሳተፉ ሠራተኞችም ሥልጠና ተሰጥቷል።

- በመረጃ ማሰባሰቡ ወቅት ከዕቃዎች ዝርዝር ውጭ የተገኙ ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን ለመልቀም የሚያስችል መመሪያና ቅጽ ተዘጋጅቶ በሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል።

- መረጃዎች ወደ ኮምፒውተር በትክክል መግባታቸውን ለመቆጣጠርና ለማረጋገጥ በተለያዩ የዳታ ኢንትሪ ሠራተኞች አንድ መረጃ ሁለት ጊዜ ወደ ኮምፒውተር እንዲገባ በማድረግና የሁሉንም የቆጠራ ቦታዎች መረጃ ወደ ኮምፒውተር በማስገባት፣ በአሁኑ ጊዜ የዳታ ክሊኒንግ ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል።

- ለሁለተኛው ዙር የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት የሚያስፈልጉ ዶክመንቶች ማለትም የመረጃ አሰባሰብና የቁጥጥር መመሪያ፣ መጠይቅ፣ የዕቃዎች ዝርዝርና ኮድ የያዘ መጽሐፍ፣ የቤተሰብ በጀት የዋጋ ጥናት መመሪያ፣ መጠይቅና የሥራ ሂደት የሚከናወንበት መርሃ-ግብር ተጠናቆና ታትሞ በሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል።

- ለዚሁ ጥናት የሚረዱ የክለሣ ጥያቄዎች ከነማብራሪያቸው፣ በጥናቱ ለተመረጡ የከተማ ቤተሰቦች በሙሉ ሊደርስ የሚችል ስለጥናቱ አጠቃላይ ግንዛቤ የሚሰጥ ደብዳቤ፣ የጥናቱን ዓላማና የሚያስገኘውን ጠቀሜታ የሚያስጨብጥ በራሪ ጽሑፍ (ብሮሽር) ተዘጋጅቶ ለቅ/ጽ/ቤቶች የተሰራጨ ሲሆን፤ የመገናኛ ብዙሃንን ተጠቅሞ

የማስተዋወቅ ተግባር ለማከናውን የሚያስችል የመግለጫ ጽሑፍ ተዘጋጅቶ መግለጫ ተሰጥቷል፡፡

- የሁለተኛው ዙር የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት የመረጃ መሰብሰብ ተግባር ከታህሣስ 28 ቀን 1997 ተጀምሮ ጥር 30 ቀን 1997 ዓ.ም ድረስ በታቀደለት መረሃ - ግብር መሠረት ተከናውኗል፡፡

- የሁለተኛው ዙር የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት መረጃ የኤዲቲንግና ኮዲንግ ተግባር በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡

2.2.3 <u>የኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጥናትን በተመለከተ</u>

- ለኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጥናት የእርማትና መለያ ቁጥር የመስጠት ተግባር ሙሉ በሙሉ ተጠናቆ በሥራ ላይ የዋለ ሲሆን፤ የዚሁ ጥናት የኮምፒውተር ኤዲት ስፔስፊኬሽን መመሪያ ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው ክፍል እንዲደርስ ተደርጓል፡፡

- የኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጥናት የሚውል የኤዲቲንግ ማንዋል ተዘጋጅቶ በሥራው ላይ ለሚሳተፉ ሠራተኞች ሥልጠና የተሰጠ ሲሆን፤ የኤዲቲንግ፣ ኮዲንግ፣ ቬሪፊኬሽን፣ ሱፐርቪዥንና መረጃ የማጥራት ሥራዎችን ለማከናወን የሚያስችል አዲስ ለተቀጠሩ ስታቲስቲሺያኖች የሦስት ቀን ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡

- የጥናቱ መረጃዎች ተቀነባብረው የሚዘጋጅበት የሠንጠረዥ ዓይነቶች (Tabulation plan) ተዘጋጅቶ በሥራ ላይ ያዋለ ሲሆን የሪፖርቱ ዝግጅት ተጠናቆ ለህትመት ተልኳል፡፡

2.2.4 <u>ልዩ ልዩ ሥራዎች</u>

- መ/ቤቱ ለሚያዘጋጀው ዓመታዊ ስታቲስቲክስ መጽሔት የሚያገለግሉ ዘርፉን የሚመለከቱ መረጃዎች ከልዩ ልዩ መ/ቤቶች ተሰብስቦና ተጠናቅሮ ለሚመለከተው ክፍል እንዲደርስ ተደርጓል፡፡

- በዋናው መ/ቤትና በቅ/ጽ/ቤቶች በኮንትራት ለተቀጠሩ ባለሙያዎች ስለ ዋጋ ጥናትና ስለ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ደህንነት ጥናት የአምስት ቀን ሥልጠና ተሰጥቷል።

- የቤተሰቦች የምግብ ፍጆታ መረጃን ወደ ሃይል ሰጪ ንጥረ ነገር (Food Energy) ለመለወጥ የሚያስችል መረጃዎችን የያዙ ዶክመንቶች ከጤናና ሥነ - ምግብ ጥናት ምርምር ተቋም በማሰባሰብ የምግብ ንጥረ ነገሮችን የመልቀም ተግባር ተከናውኗል።

- በበጀት ዓመቱ መ/ቤቱ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የኢኮኖሚ ፖሊሲና ዕቅድ መምሪያ ጋር በመደጋገፍ ተሣትፏዊ የድህነት ዳሰሳ ጥናት ለማካሄድ በታቀደው መሠረት የመ/ቤቱ ባለሙያዎች ከጥናት ዝግጅት እስከ መረጃ መሰብሰብ ድረስ በነበረው የሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሰፊ ተሣትፎ አድርገዋል። በተጨማሪም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለመስክ ሥራ የመደበውን በጀት በማስተዳደር እና ለጥናቱ የሎጂስቲክስ ድጋፍ በማድረግ ጥናቱ ስኬታማ እንዲሆን አድርጓል።

- በበጀት ዓመቱ ለማካሄድ ለታቀደው ዓለም አቀፋዊ የንፅፅር ፕሮግራም (International Comparison Program) የጥናቱን ፍሬም ዎርክ፣ በጀትና የሚስፈልገውን የሰው ኃይል እንዲሁም ጥናቱ የሚካሄድባቸውን የገጠርና የከተማ ቦታዎች የመለየት ተግባር የተጠናቀቀ ሲሆን፣ በጥናቱ የሚካተቱ የዕቃዎችና አገልግሎቶች ዓይነትና ዝርዝር ተዘጋጅቷል።

## 2.3. <u>የኢንድስትሪ፣ንግድ ትራንስፖርት መገናኛ ስታቲስቲክስ ጥናት</u>

### 2.3.1 <u>የኢንዱስትሪ ስታቲስቲክስ ጥናቶችን በተመለከተ</u>

#### ሀ. <u>የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት</u>

- በ1996 የዕቅድ ዘመን የመረጃ ማሰባሰቡ ተግባር የተጠናቀቀለት የ1995 በጀት ዓመትን የሚመለከተው የዘርፉ ጥናት የመረጃ ቅንብርና ትንተና ሥራው ተጠናቆና ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል።

- በ1997 ለተካሄደው የ1996 በጀት ዓመትን የሚመለከተው ዓመታዊ የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት የመጠይቅና የአሞላል መመሪያ ዝግጅት ተጠናቆና የመረጃ ማሰባሰቡ ሥራ ተካሂዶ የኤዲቲንግና ኮዲንግ ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡

ለ. <u>የኢኮኖሚያዊ ድርጅቶች አጠቃላይ ቆጠራ ምዝገባን በተመለከተ</u>

በ1995 በጀት ዓመት የመረጃ መሰብሰብ ሥራው የተጠናቀቀለት የኢኮኖሚ ድርጅቶች ቆጠራ ጥናት የዳታ ኢንትሪ፣ የዳታ ክሊኒንግ፣ የሠንጠረዥ ዝግጅትና የትንተና ጽሑፍ ተጠናቆ የጥናቱ ውጤት ሪፖርት ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል፡፡

ሐ. <u>የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ወቅታዊና የሩብ ዓመት የዋጋ ጥናቶችን በተመለከተ</u>

- በየሩብ ዓመቱ እንዲወጣ የሚጠበቀው የወቅታዊ የማምረቻ ድርጅቶች ጥናት የ1997 ዓ.ም የአንደኛ፣ ሁለተኛና ሦስተኛ ሩብ ዓመት ጥናት ሪፖርቱ ተጠናቆ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል፡፡ አራተኛውን ሩብ ዓመት ጥናት ለማካሄድ ዝግጅቱ እየተከናወነ ይገኛል፡፡

- የሩብ ዓመት የዋጋ ጥናትን በተመለከተ የአንደኛ፣ የሁለተኛና ሶስተኛ ሩብ ዓመት መረጃዎች ተሰብስበው የመረጃ ጥራት ፍተሻ ተካሂዶ ኢንዴክስ ለማስላት የመረጃ ቅንብር ሥራ በመካሄድ ላይ የሚገኝ ሲሆን አራተኛውን ዙር የዋጋ መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችል የዝግጅት ሥራ ተጠናቋል፡፡

መ. <u>የውጭ ንግድ መረጃን በተመለከተ</u>

እ.ኤ.አ የ2004 የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት የውጭ ንግድ መረጃን በተመለከተ የመረጃ ቅንብር ሥራው ተጠናቋል፡፡

ሠ. ሌሎች የተከናወኑ ተግባራት

- መ/ቤቱ ለሚያዘጋጀው ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሔት ዘርፉን የሚመለከቱ መረጃዎች ከሚመለከታቸው መ/ቤቶችና ድርጅቶች ተሰብስበውና ተጠናቅረው ለሚመለከተው ክፍል ተልከዋል፡፡

- በቅርቡ ሊካሄድ ለታቀደው የግማሽ ዓመት የንግድና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ጥናት መጠይቅና የአሞላል መመሪያ ዝግጅት ተጠናቆ በሙከራ ደረጃ ጥናቱን ለማካሄድ ቅድመ ዝግጅት በመካሄድ ላይ ነው፡፡

- የትራንስፖርትና መገናኛ መጽሔትን ለማሻሻል የሚያስችል ጥናት በማካሄድ ላይ ይገኛል፡፡

## 2.4 የማህበራዊ ስታቲስቲክስን በተመለከተ

### 2.4.1 የሰው ኃይል ስታቲስቲክስ

- ሁለተኛው ዙር ተከታታይ የሥራ ስምሪት ጥናትን በሚመለከት የተሰበሰቡ መረጃዎችን የማጥራት ሥራና የዳታ ኢንትሪ፣ ቬሪፊኬሽን፣ የክሊኒንግ ሥራና የጥናቱ ግኝትም ግምገማ ተካሂዶና ሪፖርቱ ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል፡፡

- የ1997 የሰው ሃይል ጥናትን በተመለከተ ጠቃሚ የሆኑ ዶኩሜንቶች የተሰበሰቡ ሲሆን፣ በጥናቱ የሚካተቱ variables ተጠናቆ በሥራ ላይ ውሏል፡፡

- የ1997 ዓ.ም የሰው ኃይል ጥናት መጠይቅ ተዘጋጅቶ በመስክ የሙከራ ጥናት ከታህሣስ 1 ቀን 1997 ዓ.ም እስከ ታህሣስ 4 ቀን 1997 ዓ.ም ድረስ የተካሄደ ሲሆን፣ ከሙከራ ጥናት በኋላ ከመረጃ ተጠቃሚዎች ጋር ታህሣስ 14 ቀን 1997 ዓ.ም የግማሽ ቀን ውይይት ተካሂዷል፡፡

- በ1997 ዓ.ም ለሚካሄደው የሰው ኃይል ጥናት ሙያዊ ድጋፍ ለመስጠት ከመጡ አማካሪ ጋር በመወያየትና ከመረጃ ተጠቃሚዎች በተገኙ አስተያየቶች የጥናቱ መጠይቅ እንዲዳብር ከመደረጉም በላይ፣

ስለwage indexእና ስለ ቀጣይ የተከታታይ ስራ ስምሪት ጥናት ከባለሙያው ጋር ምክክር ተደርጓል፡፡

- ለ1997 የሰው ኃይል ጥናት የሚያገለግል የመረጃ ሰብሳቢዎችና የተቆጣጣሪዎች መመሪያ፣ የoccupation እና ኢንዱስትሪ ኮድ ቡክ በአራት ዲጂት ተዘጋጅቶ በሥራ ላይ ውሏል፡፡

- የ1997 የሰው ኃይል ጥናት መረጃ ከመስክ ተሰብስቦ ከሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች መረጃ የተሰበሰበባቸው መጠይቆች ወደ ዋናው መ/ቤት ተመልሰዋል፡፡ ለዚሁም ሥራ የሚያገለግል የቅድመ ሪፖርት ዝግጅትን በተመለከተ ምስል ሠንጠረዥ ዝግጅት /Dummy tables/ በአብዛኛው ተከናውኗል፡፡

- ለጥናቱ የሚሆን የኤዲቲንግና ኮዲንግ መመሪያ ዝግጅት እንዲሁም መጠይቁን ወደ እንግሊዘኛ የመተርጎም Edit Specification እና Derived Variables እና Logical Relationship ሥራ ተጠናቆ የመረጃ ቅንብር ለመጀመር ዝግጁ ሆኗል፡፡

### 2.4.2 የትምህርት፣ ባህልና ስፖርት ስታቲስቲክስን በተመለከተ

- በ1996 ዓ.ም ለመ/ቤቱ ዓመታዊ ስታቲስቲክስ መጽሔት ዝግጅት የሚያስፈልጉ መረጃዎች ከክልል ተሞልተው የመጡ መጠይቆች ተፈትሸው የታዩ ጉድለቶች እንዲስተካከሉና በሌላ ጊዜ እንዳይደገሙ በጥራዝ ተዘጋጅተው ለሚመለከታቸው የስታቲስቲክስ ቅ/ጽ/ቤቶች ተልኳል፡፡ እንዲሁም ስለመጠይቆቹ አሞላል ማብራሪያ የተሰጠ ሲሆን፣ መረጃዎች በመጠይቅ ተሞልተው ሲመጡ ወደ ኮምፒውተር የሚገቡበትና ለተጠቃሚዎች በሚያመች መልክ ተዘጋጅተው የሚቀርቡበት ሠንጠረዥ ተዘጋጅቷል፡፡

- ለወላጅ አልባ ህፃናት ጥናት የሚያገለግል የመጀመሪያ ረቂቅ ዶክሜንት ተዘጋጅቶ፣ ረቂቅ መጠይቅ ዝግጅት የተጀመረ ቢሆንም መ/ቤቱ ባለበት የሰው ኃይል ዕጥረት እንዲሁም ጥናቱ አዲስ በመሆኑ የሜቶዶሎጂና የመረጃ አሰባሰብ አፈፃፀም ላይ ተጨማሪ ዝግጅቶች በማስፈለጉ ጥናቱ በሌላ ጊዜ እንዲከናወን ተደርጓል፡፡

- ከአስተዳደራዊ መዛግብት ሊሰበሰቡ የሚችሉ መረጃዎችን በወረዳ ኔት ለማገናኘት በታቀደው መሠረት ከተለያዩ ክልሎች የተሰበሰቡ የትምህርት፣ የባህልና የስፖርት መረጃዎችን የያዙ መጠይቆች ተፈትሸው ለ1997 ዓ.ም መረጃ የሚሰበሰብባቸው ቅጾች ተዘጋጅተው ለሚመለከተው ክፍል ተሰጥቷል።

- ከ1998 እስከ 2002 ዓ.ም በትምህርት፣ በስፖርትና በባህል መስክ ለመሰብሰብ የታቀዱትን የመረጃ ዝርዝሮች /የአምስት ዓመት የሥራ መርሃ - ግብር/ የያዘ ዶክመንት የተዘጋጀ ሲሆን ለBPR ዝግጅት ግብዓት ሆኖ አገልግሏል።

- በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የባህል መረጃን ለመሰብሰብ በተደረገው ጥረት በአራት ክፍለ ከተሞች የተሰበሰበ ሲሆን፤ በቀበሌዎች መታጠፍ ምክንያት በቀሪዎቹ ክፍለ ከተሞች መጠይቆቹን መሰብሰብ አልተቻለም።

### 2.4.3 የሕግና ደንብ ስታቲስቲክስን በተመለከተ

- የ1996 ዓ.ም የሕግና ደንብ መረጃዎችን በተሟላ ሁኔታ ለመሰብሰብ እንዲቻል መጠይቆች ተዘጋጅተው ለክልል ቢሮዎችና ለፌዴራል መ/ቤቶች ተልከዋል። እንዲሁም መረጃዎች ወደ ኮምፒውተር የሚገቡበት ሁኔታ በሚያመች መልክ ተዘጋጅተው የሚቀርቡበት ሠንጠረዥ ተዘጋጅቷል። በተጨማሪም ከክልል ተሞልተው በመጡ መጠይቆች ላይ የታዩ ጉድለቶች በአንድ ጥራዝ ተዘጋጅቶ ለቅ/ጽ/ቤቶች የተሰጠ ሲሆን ስለመጠይቆች አሞላል ማብራሪያ ተሰጥቷል።

- የኢትዮጵያን Gender status index (GSI) ለማዘጋጀት የሚያስፈልጉ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን ለማጠናቀር ለተቋቋመው ግብረ-ሃይል አስፈላጊው ድጋፍ ተሰጥቷል።

- የጐዳና ተዳዳሪ ልጆች ጥናት ለማካሄድ የሚያስችል ፕሮፖዛል ተዘጋጅቶ የቀረበ ሲሆን፤ መ/ቤቱ በገጠመው የሰው ኃይል ዕጥረትና በጥናቱ አዲስነት መከተል ያለበትን የአጠናን ዘዴ እንደገና መፈተሽ በማስፈለጉ በዚህ ዓመት ጥናቱን ማካሄድ አልተቻለም።

### 2.4.4 ሌሎች ሥራዎችን በተመለከተ

- ለሌሎች መ/ቤቶችና ድርጅቶች የመረጃና የቴክኒክ ድጋፍ ተሰጥቷል።

- በኤች.አይ.ቪ. /ኤድስና ሌሎች የአባለዘር በሽታዎችን በተመለከተ በበጀት ዓመቱ መ/ቤቱ ከጤና ጥበቃ ሚ/ር፣ ከኤች.አይ.ቪ. /ኤድስ ብሔራዊ ጽ/ቤት፣ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የጤና አጠባበቅ ትምህርት ክፍልና ከጤና አጠባበቅ ባለሙያዎች ማህበር ጋር ሊካሄድ ለታሰበው Behavioral Surveillance Survey (BSS) ጥናት የበጀት ዝግጅት የተደረገ ሲሆን፣ የመጠይቅ ዝግጅት፣ በመረጃ ሰብሳቢዎችና የተቆጣጣሪዎች መመሪያ ዝግጅቶች የሙከራ ጥናት ላይ ተሳትፎ ተደርጓል። በተጨማሪም በመስክ ላይ ለሚሠማሩ መረጃ ሰብሳቢዎች በመ/ቤቱ ሠራተኞች ሥልጠና ተሰጥቷል።

## 3. የ1997 በጀት ዓመት የፊዚካል ሥራ አፈጻጸም

በ1997 በጀት ዓመት መ/ቤቱ ለሚያካሂዳቸው አዳዲስ ጥናቶችንና ከ1996 የተሸጋገሩ ቀሪ ሥራዎችን ለማከናወን በዕቅድ መያዙንና በበጀት ዓመቱ ያከናወናቸዉን ሥራዎች በዝርዝር ቀርበዋል። የእነዚህን ጥናቶች የፊዚካል አፈፃፀም በተመለከተ ደግሞ በሚቀጥለው ሠንጠረዥ ቀርቧል።

ሠንጠረዥ 1 በ1997 በጀት ዓመት የፊዚካል ሥራ አፈጻጸም

| ተ.ቁ | የጥናቱ ዓይነት | ጥናቱ የሚገኝበት ደረጃ | እስከ 1997 በጀት ዓመት መጨረሻ የተከናወነ | የ1997 በጀት ዓመት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም |
| 1 | የ1997 የግብርና ናሙና ጥናት | | | | | |
| 1.1 | የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት | አዲስ | 6.43 | 93.57 | 93.57 | 100 |
| 1.2 | የግብርና ምርት ናሙና ጥናት የመኸር ወቅት | | | | | |
| | • የታረሰ መሬት ናሙና ጥናት | አዲስ | 6.43 | 93.57 | 93.57 | 100 |
| | • የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ | አዲስ | 6.43 | 93.57 | 93.57 | 100 |
| | • የመሬት አጠቃቀም | አዲስ | 6.43 | 93.57 | 93.57 | 100 |
| 1.3 | የቤት እንስሳት፣ ዶሮና የንብ ቀፎዎች ጥናት | አዲስ | 6.43 | 83.57 | 83.57 | 100 |
| 1.4 | የግብርና ምርት ናሙና ጥናት የበልግ ወቅት | አዲስ | 6.43 | 83.57 | 83.57 | 70 |
| 1.5 | የሰፋፊና መካከለኛ የድርጅት እርሻዎች ጥናት | አዲስ | 6.43 | 83.57 | 83.57 | 100 |
| 1.6 | የአትክልትና ሥራ ሥር ተክሎችና የቋሚ ሰብል ምርት ጥናት | አዲስ | 7.50 | 57.50 | 57.50 | 100 |
| 1.7 | የ1996 የግብርና ምርት ናሙና ጥናት በበልግ ወቅት | ነባር | 65.00 | 35.00 | 35.00 | 100 |
| 1.8 | የ1996 ሰፋፊና መካከለኛ የድርጅት እርሻዎች ጥናት | ነባር | 65.00 | 35.00 | 35.00 | 100 |
| 2 | የግብርና ዉጤቶች የአምሮቾች ዋጋ ጥናት | አዲስ | 9.00 | 91.00 | 91.00 | 100 |
| 3 | የችርቻሮ ዋጋ ጥናት | አዲስ | 15.00 | 85.00 | 85.00 | 100 |
| 4 | የኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጥናት | ነባር | 60.00 | 40.00 | 36.00 | 90 |
| 5 | የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት 1ኛ ዙር | ነባር | 60.00 | 40.00 | 26.00 | 65 |
| 6 | የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት 2ኛ ዙር | አዲስ | - | 100.00 | 65.00 | 65 |
| 7 | ወቅታዊ የማምረቻ፣ የንግድ አገል/ሰጪ ድርጅት* | አዲስ | - | 100.00 | 100.00 | 100 |
| 8 | የማምረቻ ኢንድስትሪ የምርት ዋጋ ኢንዴክስ | አዲስ | - | 72.52 | 72.52 | 100 |
| 9 | የ1995 የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱ.ጥናት | ነባር | 70.00 | 30.00 | 35.00 | 100 |
| 10 | የ1996 የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱ.ጥናት | አዲስ | - | 65.00 | 65.00 | 100 |
| 11 | የቢዝነስ ምዝገባ ሥርዓት ሥራዎች | ነባር | 65.00 | 35.00 | 35.00 | 100 |
| 12 | የሰው ኃይል ጥናት | አዲስ | - | 75.00 | 65.00 | 87 |
| 13 | ተከታታይ የሥራ ስምሪት ጥናት*** | ነባር | 83.00 | 17.00 | 17.00 | 100 |

*** መ/ቤቱ በገጠመው የሰው ኃይል ዕጥረትና በመረጃ አሰባሰብ አፈፃፀም ላይ ተጨማሪ ዝግጅት ማድረግ በማስፈለጉ ምክንያት በዚህ በጀት ዓመት ጥናቶቹ አይካሄዱም።

4. <u>ሣምፕሊንግ ሜቶዶሎጂን በተመለከተ</u>

- የ1997 ዓ.ም የቋሚ ሰብል የአትክልትና ሥራ ሥር ጥናት የናሙና ቆጠራ ቦታዎች ምርጫ፣ የአመዘጋገብና አመራረጥ መመሪያ ተዘጋጅቷል። መመሪያውንም መሠረት በማድረግ የቤተሰብን አመዘጋገብና የናሙና ቤተሰቦች አመራረጥን በተመለከተ ለአሠልጣኞች ሥልጠና ተሰጥቷል።

- ለ1997 የግብርና ናሙና ጥናት ለተመረጡ ቤተሰቦች ማስተላለፊያ ቅጽና በትንበያ ጥናት የሚያስፈልጉ የናሙና ቤተሰብ አመራረጥ መመሪያ ተዘጋጅቷል። ስለተዘጋጀው መመሪያና አዳዲስ ስለሚገኙ ባለይዞታዎች አመዘጋገብ በዋናው መ/ቤት ለአሰልጣኞች ስልጠና ተሰጥቷል። በተጨማሪም የኮድ ቡክ ተዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው ክፍሎች ተሠራጭቷል።

- የ1997 የሰብል ትንበያ ጥናትን በሚመለከት በቅጾቹ የተሞሉ የአካባቢ መለያ ስምና ኮድ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የክትትልና የቁጥጥር ሥራ ተካሂዷል። እንዲሁም በድጋሚ ለተሠራው ጥናት ግምት በማዘጋጀት ከሚመለከተው መምሪያ ጋር ውጤት እንዲወጣ ተደርጓል።

- ለ1996 ዓ.ም የበልግ ወቅት የግብርና ናሙና ጥናት የweight ዝግጅት ሥራ የተጠናቀቀ ሲሆን፤ የጥናቱ የ CV ግምገም ተካሄዶና የሜቶዶሎጂ ሪፖርትም ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው ክፍል ተሰጥቷል።

- የ1996 ዓ.ም የሠፋፊና መካከለኛ እርሻዎች ጥናት የአካባቢ መለያ ሥምና ኮድ ትክክለኛነት የመከታተልና የእርማት ሥራ የተከናወነ ሲሆን፤ የሜቶዶሎጂ ሪፖርትም ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው ክፍል ተሰጥቷል።

- የ1997 የሰብል ምርትና የታረሰ መሬት ስፋት ጥናት weight እና Rate ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው ክፍል ተልኳል።

- የ1997 የቤት እንስሳት ጥናት weight እና Rate እንዲሁም የሜቶዶሎጂ ሪፖርት ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው ክፍል የተላከ ሲሆን፤ የውጤት ትክክለኛነት ግምገማም ተከናውኗል።

- የ1997 ዓ.ም የሰብል ትንበያ ጥናትን አስመልክቶ የውጤት አስተማማኝነት (CV) ግምገማ የተካሄደ ሲሆን፣ የሜቶዶሎጂ ሪፖርትም ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው ክፍል ተላልፏል።

- ለ1997 ዓ.ም ሠፋፊና መካከለኛ እርሻዎች ጥናት የሚጠኑ ድርጅቶች ዝርዝር ለቅ/ጽ/ቤቶች የተላከ ሲሆን፣ የእርሻዎቹን ፍሬም በአዲስ መልክ ለማዘጋጀት ዝርዝሩን ወደ ኮምፒውተር የማስገባት ሥራ ተካሂዷል።

- ለ1996 ዓ.ም የኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጥናት ለሁሉም ክልሎች Weight እና Rate ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው ክፍል ተሰጥቷል።

- የ1997 ሰፋሪዎች ጥናትን ለማከናወን የሚያስችል የመመዝገቢያና የምርጫ ቅጽ ተዘጋጅቶ ለቅ/ጽ/ቤቶች የተላከ ሲሆን፣ weight እና Rate ለማዘጋጀት የሚያስፈልገው የቅድመ ዝግጅት ሥራም ተከናውኗል።

- ለ1997 የሰው ኃይል ጥናት የዲዛይን ዝግጅት፣ ናሙና መረጣ፣ የአመዘጋገብና የአመራረጥ መመሪያ ዝግጅት ሥራዎች ተከናውነዋል። እንዲሁም weight እና Rate ለማዘጋጀት የሚያስፈልገው የቅድመ ዝግጅት ሥራም ተከናውኗል።

- የአምራቾች ዋጋ ኢንዴክስን ለማዘጋጀት የሚረዳ ስለ መረጃ አሰባሰብ፣ ስለናሙና ድርጅቶችና ምርቶች አመራረጥ የቴክኒክ ድጋፍና አስተያየት የተሰጠ ሲሆን፣ ለተሳትፎአዊ የድህነት ዳሰሳ ጥናት የቆጠራ ቦታዎች ምርጫ ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን ለማከናወን ተችሏል።

- የኢኮኖሚያዊ ድርጅቶች ቆጠራ ውጤት መረጃው ለቀጣይ የከተማ ጥናቶች እንደፍሬም የሚያገለግል በመሆኑ መረጃውን ከዚህ በፊት ከነበረው መረጃ ጋር የማገናዘብና የማጥራት ሥራ በአብዛኛው ተጠናቋል።

- የዓለም አቀፍ የዋጋ ንፅፅር (ICP) ጥናት ለማካሄድ የሚያስችል የናሙና ብዛቶችንና አመራረጥ ዘዴ ሥራ ከሚመለከተው ክፍል ጋር በመሆን ተከናውኗል።

- የ1997 ዓ.ም የመጀመሪያ እና የሁለተኛው ሩብ ዓመት የወቅታዊ የማምረቻ፣ የንግድና የአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ጥናት Weight እና Rate የተዘጋጀ ሲሆን፤ የሜቶዶሎጂ ሪፖርትም ተጠናቆ ለሚመለከተው ክፍል ተላልፏል፡፡

- በሁለተኛው ዙር የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት ወቅት በማይገኙ ቤተሰቦች የሚተኩትን ለመምረጥ የሚያስችል መመሪያ ተዘጋጅቶ ለቅ/ጽ/ቤቶች ተልኮ በሥራ ላይ ውሏል፡፡

- የኤች.አይ.ቪ. /ኤድስ ባህርይ ቅኝት ጥናት ለማካሄድ የዲዛይን ዝግጅት እና የአመዘጋገብና የአመራረጥ መመሪያ ዝግጅት ሥራ ተከናውኗል፡፡

- በመሥሪያ ቤት ደረጃ የኢንዱስትሪና የሙያ ምደባ ወጥ የሆነ ረቂቅ ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው መምሪያዎች ተላልፏል፡፡

- በመካከለኛ ዘመን የስታቲስቲክስ ፕሮግራም ዘመን ሊሸፈኑ ከታሰቡ የመረጃ ክፍተቶች በመነሳት በሁሉም የኢኮኖሚ ዘርፎች ከአስተዳደራዊ ማዛግብት ሊገኙ የሚችሉ መረጃ አይነቶች ተሰብስበውና ተጠናቅረው ለሚመለከታቸው ተሰጥቷል፡፡

- በየሴክተሩ የሚሰበሰቡትን መረጃዎች በተመለከተ ከፌዴራል የመንግስት መሥሪያ ቤቶች በምን መልክ እንደሚገኙ፣ ከየትኛው መ/ቤት ሊገኙ እንደሚችሉ፣ በዓመት ውስጥ በምን ያህል ድግግሞሽ ሊገኙ እንደሚችሉና የሚጠቀሙባቸው ዕንስ ሐሳቦችና ፍቺዎች መረጃ ከ31 መ/ቤቶች መረጃ ተሰብስቧል፡፡ እንዲሁም ከፌዴራል መ/ቤቶች ሊገኙ የማይችሉትን የመረጃ ዓይነቶች በናሙና በተመረጡ ክልሎችና ወረዳዎች ከሚገኙ የመንግሥት መ/ቤቶች በምን መልክ እንደሚገኙ፣ በምን ያህል ድግግሞሽ ሊገኙ እንደሚችሉና የሚጠቀሙባቸው ዕንስ ሐሳቦች ምን እንደሆኑ የሚያሳይ መረጃ ከ 3 ክልሎች ከሚገኙ ከ15 በላይ የክልልና የወረዳ ቢሮዎች ተሰብስቧል፡፡

- ከፌዴራል የመንግሥት መ/ቤቶችና፣ ከክልልና ከወረዳ መ/ቤቶች እንዲሁም ከተለያዩ ምንጮች የሚገኙ በየሴክተሩ ያሉ ዕንስ ሐሳቦችና ፍቺዎች በተጨማሪ ከተለያዩ ምንጮች (ከኢንተርኔት፣ ከተባበሩት

መንግሥታት ድርጅቶች ዶክመንቶች ወዘተ) እንዲሁም ፎርማቶች በእንግሊዝኛና በአማርኛ ቋንቋ እየተዘጋጀ ይገኛል፡፡

- በ1997 ከፌዴራል የመንግሥት መ/ቤቶች፣ በናሙና ከተመረጡ ክልሎችና ወረዳዎች ሊገኙ የሚችሉ የመረጃ ዓይነቶችን ለስታቲስቲክስ ጠቀሜታ ሊውሉ በሚችሉበት ፎርማት የተዘጋጁትን በመገምገም ፎርማቶች በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋ እየተዘጋጁ ይገኛሉ፡፡

- በተለያዩ ክልሎች በሚገኙ 8 ዞኖች ውስጥ የ24 ወረዳዎችን ለሁለት የመክፈል ወይም የማጣመር ሥራ የብሉ ፕሪንት ሽንሽና ተሰርቶ ለንድፍ ሥራ ተዘጋጅቷል፡፡ እንዲሁም በ10 ዞኖች ውስጥ ለሚገኙ 34 ወረዳዎችና 10 የቆጠራ ቦታዎች UTM ገብቶላቸው በGIS ለመሥራት የቅድመ ዝግጅት ሥራ ተጠናቋል፡፡

- በኢኮኖሚያዊ ድርጅቶች ቆጠራ ወቅት ወቅታዊ የተደረጉ የከተማ የቆጠራ ቦታ ካርታዎችና የድንበር መግለጫዎች በካርታ ሥራ ጊዜ ከተሰራው ጋር በማገናኘት የማደራጀት ሥራ የሁሉም ክልሎች ተጠናቋል፡፡

- በደቡብ ህዝቦች ክልል በተከሰተው የአስተዳደር ለውጥ ምክንያት የወላይታና ዳውሮ ዞኖች የወረዳ ካርታዎች የማስተካከል ሥራ ተጠናቋል፡፡ እንዲሁም በዚሁ ክልል የሃዲያ፣ የከምባታና ጠንባሮ፣ የአላባ፣ የጉራጌ፣ የቤንች ማጂና የከፋ ዞኖች የንድፍ ሥራ ለመሥራት በብሉ ፕሪንት ላይ የሽንሽና ሥራ ተከናውኗል፡፡

- በ1997 መ/ቤቱ ለሚያካሂደው የቋሚ ሰብሎች፣ የአትክልትና ሥራ ሥር ተክሎች ምርታማነት ጥናት 190 የቆጠራ ቦታ ካርታዎች ተዘጋጅተው የተሠራጩ ሲሆን፤ ከመ/ቤቱ ውጭ ለመጡ የካርታ ተጠቃሚዎች 140 የወረዳ ካርታዎችና 293 የቆጠራ ቦታ ካርታ ሽያጭ ተፈጽሟል፡፡ እንዲሁም የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ለሚያካሂደው የሥነ - ሕዝብና ጤና ጥናት የሚውል የ258 ገጠርና የ195 የከተማ በድምሩ 453 የካርታ ኮፒዎች ተዘጋጅተው ተሰጥተዋል፡፡ በ1997 ለሚካሄደው የሰው ኃይል ጥናት 995 እና

ለኤች.አይ.ቪ /ኤድስ ባህርይ ቅኝት ጥናት 120 የካርታ ኮፒዎች ተዘጋጅተው ተሰጥተዋል።

## 5. የአካባቢ ጽ/ቤቶችና የመስክ ስራ ክንውን ተግባራትን በተመለከተ

### 5.1 የሰው ኃይል ስልጠና

- የ1997 ዓ.ም የቅድመ ማስጠንቀቂያ የሰብል ምርት ግምገማ፣ ለዋናው መኸር ግብርና ናሙና ጥናት፣ ለቤት እንስሳት ጥናት፣ ለበልግ ወቅት ግብርና ናሙና ጥናትና ለስፋፊና መካከለኛ እርሻዎችን በተመለከተ በሐምሌ ወር 1996 ዓ.ም የአሠልጣኞች ስልጠና እንዲሁም በነሐሴ ወር 1996 ዓ.ም ደግሞ በ25ቱ ቅ/ጽ/ቤቶች ለሚገኙ የመስክ ሠራተኞች ሥልጠና ተሰጧል።

- የአትክልት፣ ሥራ ሥርና ቋሚ ሰብሎች የናሙና ጥናት ከተፈጥሮ ሀብትና ግብርና መምሪያ በተውጣጡ ባለሙያዎች ብዙዎቹን ቅ/ጽ/ቤቶች ያማክላሉ ተብለው በተመረጡት በጅማ፣ አዋሣ፣ ጎንደር፣ ናዝሬት፣ ሐረር ስታቲስቲክስ ቅ/ጽ/ቤቶች የመስክ ሠራተኞችን በማሰባሰብ ሥልጠና ተሰጧል።

- በሁለተኛው ዙር የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት ላይ ለሚሣተፉ የመስክ ሠራተኞች የአሰልጣኞች ስልጠና በዋናው መ/ቤት ከህዳር 16 እስከ ኅዳር 30 ቀን 1997 ዓ.ም የተሰጠ ሲሆን፤ በተመሣሣይ በቅ/ጽ/ቤቶች ከታህሣስ 4 ቀን እስከ ታህሣስ 23 ቀን 1997 ዓ.ም ድረስ ለመስክ ሠራተኞች የንድፈ ሃሳብና የተግባር ስልጠና ተሰጧቸው ወደ ሥራ ተሰማርተዋል።

- በ25ቱ ቅ/ጽ/ቤቶች አዲስ ለተቀጠሩ 75 ስታቲስቲሺያኖች ስለግብርና ጥናት ዓላማዎች ጥቅም ላይ ስለሚውሉ መጠይቆችና መመሪያዎች እንዲሁም በፅንሰ ሃሳብና ፍችዎቻቸው የአንድ ሳምንት ሥልጠና ተሰጧል።

- የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ወቅታዊ ጥናት በየሩብ ዓመቱ በተመረጡ ኢንዱስትሪዎች ላይ እንዲካሄድ በተወሰነው መሠረት ጥናቱን ለማካሄድ ከቅ/ጽ/ቤት ለተውጣጡ በሥራው ለሚሰማሩ የመስክ ሠራተኞች በዋናው መ/ቤት ሥልጠና እንዲሰጥ ተደርጓል።

- በ1997 ዓ.ም ለተካሄደው የሰው ኃይል ጥናት የአሰልጣኞች ሥልጠና ከየካቲት 7 ቀን 1997 ዓ.ም እስከ የካቲት 14 ቀን 1997 ዓ.ም ድረስ በዋናው መ/ቤት የተከናወነ ሲሆን፣ በተመሣሣይ ሁኔታ ይኸው ሥልጠና ለመስክ ሠራተኞችና መረጃ ሰብሳቢዎች ከየካቲት 18 ቀን 1997 ዓ.ም እስከ የካቲት 27 ቀን 1997 ዓ.ም ድረስ በቅ/ጽ/ቤቶች ተሰጥቷል፡፡

## 5.2 የቅ/ጽ/ቤቶች የሰው ኃይልን በተመለከተ

- ባለፉት ተከታታይ ዓመታት የቅ/ጽ/ቤት የኃላፊነት ቦታን በፕሮፌሽናል ለማስያዝ መ/ቤቱ በተደጋጋሚ ጊዜ በደረጃ ዕድገትና በቅጥር ያደረገው ሙከራ አጥጋቢ ውጤት ያላስገኘለት ነበር፡፡ በበጀት ዓመቱ መ/ቤቱ ያሉትን ባለሙያዎች በጊዜያዊነት በመመደብ ሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች በፕሮፌሽናሎች እንዲመሩ አድርጓል፡፡

- የቅ/ጽ/ቤቶችን የሰው ኃይል በባለሙያዎች ለማሟላት በተደረገ ጥረት ቋሚ ስታቲስቲሽያኖች ከፕሣ-1 እስከ ፕሣ-4 የሥራ መደቦች በዕድገትና በቅጥር እንዲሟሉ የተደረገ ሲሆን፣ በበጀት ዓመቱ ለሚካሄዱ ጥናቶችም በኮንትራት የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው 45 ባለሙያዎች ተቀጥረው ጽ/ቤቶቹን በማገልገል ላይ ይገኛሉ፡፡

## 6. መረጃ ማቀነባበርን በተመለከተ

## 6.1 የኤዲቲንግና ኮዲንግ

ከሐምሌ 1 ቀን 1996 እስከ ሰኔ 30 ቀን 1997 ዓ.ም ድረስ የመረጃ መሰብሰብ ተግባር ለተከናወነላቸው የ1996 የበልግ ወቅት የግብርና ናሙና ጥናት፣ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጥናት፣ የኢኮኖሚ ድርጅቶች ምዝገባ፣ ተከታታይ የሥራ ስምሪት ጥናት (ሁለተኛ ዙር)፣ የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት (አንደኛ ዙር) እንዲሁም የ1997 የሰብል ትንበያ ጥናት፣ የቤት እንስሳት ጥናት፣ የመኸር ወቅት የመሬት ስፋትና የእርሻ ሥራ ጥናት፣ የሰብል ግምገማ ጥናት፣ የታረሰ መሬት ስፋትና ምርት መጠን ጥናት፣ የሠፈራ ጣቢያ እርሻ ሥራ ጥናት ወርሃዊ የዋጋ ጥናቶችና የቤተሰብ ገቢ፣ፍጆታና ወጪ ጥናት (ሁለተኛ ዙር) የበልግ ጥናት የኤዲቲንግና ኮዲንግ ሥራ ተከናውኗል፡፡

## 6.2 የዳታ ኢንትሪና ክሊኒንግ

በ1997 የዕቅድ ዘመን የመረጃ መሰብሰብ ተግባራቸው በ1996 ዓ.ም እና በ1997 ዓ.ም የተከናወነላቸው የ1995 ዓ.ም የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት፣ የ1996 የበልግ ወቅት የግብርና ናሙና ጥናት፣ የሠፋፊና መካከለኛ እርሻዎች ጥናት፣ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጥናት፣ የኢኮኖሚ ድርጅቶች ምዝገባ፣ ተከታታይ የሥራ ስምሪት ጥናት (ሁለተኛ ዙር)፣ የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት (አንደኛ ዙር) እንዲሁም የ1997 የሰብል ትንበያ ጥናት፣ የቤት እንስሳት ጥናት፣ የመኸር ወቅት የመሬት ስፋትና የእርሻ ሥራ ጥናት፣ የሰብል ግምገማ ጥናት፣ የታረሰ መሬት ስፋትና ምርት መጠን ጥናት፣ የሠፊራ ጣቢያ እርሻ ሥራ ጥናት፣ የመጀመሪያው ሩብ ዓመት የትላልቅና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች ጥናት፣ ወርሃዊ የዋጋ ጥናቶችና የቤተሰብ ገቢ፣ፍጆታና ወጪ ጥናት (1ኛ ዙር) መረጃ ወደ ኮምፒውተር የማስገባትና የማጥራት ሥራ ተካሂዶላቸዋል:: በተጨማሪም የቤተሰብ ገቢ ወጪና ፍጆታ ጥናት 1ኛ ዙርና ሁለተኛ ዙር የክሊኒንግ ሥራ ተጀምሯል::

## 6.3 የሠንጠረዥ ዝግጅት

በዕቅድ ዘመኑ ውስጥ የጥናቶችን ሪፖርት ለማዘጋጀት የሚያስፈልጉ የኮምፒውተር ፕሮግራሞች ተዘጋጅተውና የጥናቱን ውጤት የሚያሣይ ሠንጠረዦች ተቀነባብረው ለሚመለከተው ክፍል የተላለፉ ሲሆን፤ ጥናቶቹም የ1996 የመኸር ወቅት አጠቃላይ የእርሻ ሥራ ሁኔታ፣ ወርሃዊ የዋጋ ጥናቶች፣ የኢንዴክስ መረጃና የ1996 ተከታታይ የሥራ ሥምሪት ጥናት (ሁለተኛው ዙር)፣ የ1995 የትላልቅና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች ጥናት፣ የ1996 የኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጥናት፣ የ1997 የሰብል ትንበያ ጥናት፣ የ1996 የበልግ ጥናት፣ የሰፋፊና መካከለኛ እርሻዎች ጥናት፣ የኢኮኖሚ ድርጅቶች ምዝገባ፣ የ1997 የቤት እንስሳት ጥናትና የ1997 የመጀመሪያው ሩብ ዓመት የትላልቅና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች ጥናት፣የመኸር ወቅት አጠቃላይ የእርሻ ሥራ ሁኔታ ጥናት፣ የታረሰ መሬት ስፋትና የምርት መጠን ጥናት የሠፊራ ጣቢያዎች የታረሰ መሬት ስፋትና የምርት መጠን ናቸው::

## 6.4 መረጃዎችን ወደ SPSS Format መለወጥ

ለበርካታ ዓመታት በመ/ቤቱ የተከማቹ የቆጠራና የናሙና ጥናት መረጃዎችን ለመረጃ ተጠቃሚዎች አመቺ በሆነ የመረጃ ማከማቻ መንገድ ለማከማቸት ጥረት የተደረገ ሲሆን፤ በ1997 የዕቅድ ዘመን የ1987 ሕዝብና ቤት ቆጠራ፣ የ1994 የግብርና ናሙና ቆጠራ፣ የ1996 የግብርና ናሙና ጥናቶች፣ ከ1989 እስከ 1995 ድረስ ያሉ የትላልቅና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች ጥናት፣ የ1995 የአነስተኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት፣ የአከፋፋይ ንግድ ጥናት፣ የ1989 እና የ1995 መደበኛ ያልሆነ የሥራ ዘርፍ ጥናቶች፣ የ1995 የጐጆ ኢንዱስትሪ ጥናት፣ ከ1990 እስከ 1995 ድረስ ያለው የሸማቾች ዋጋ ጥናት፣ ከ1989 እስከ 1996 ድረስ ያለው የአምራቾች ዋጋ ጥናት፣ የ1988 የ1990 እና የ1992 የኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጥናት፣ የ1996 ተከታታይ የሥራ ስምሪት ጥናት፣ ሁለተኛ ዙር የ1990 የጤናና አመጋገብ ጥናትና የ1992 የዲሞግራፊና ጤና ጥናት የ1996 የሶማሌና የአፋር የቤት እንስሳት ጥናት፣1997 የመኸር አጠቃላይ የእርሻ ሥራ ሁኔታ ጥናት የሚጠቀሱ ናቸው።

## 6.5 ሌሎች ሥራዎች

- በበጀት ዓመቱ መ/ቤቱ ለመንግሥት መ/ቤቶች፣ በድርጅቶችና በቤተሰብ ደረጃ ከተለያዩ መረጃ ተጠቃሚዎች በቀረበው ጥያቄ መሠረት የተለያዩ ጥናቶችና ቆጠራዎች ጥሬ መረጃዎችና የሪፖርት ሠንጠረዦች ተዘጋጅተው ተሰጥተዋል።

- እ.አ.አ. የ1996፣ 1998 እና የ2000 የኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጥናቶች መረጃ Indicators በEthioInfo Databases system የማዘጋጀቱ ሥራ ተጠናቋል።

- እ.አ.አ የ1996 እና የ2000 የቤተሰብ ገቢ፣ፍጆታና ወጪ ጥናቶች መረጃ Indicators በEthioInfo Databases የማዘጋጀቱ ሥራ ተጠናቋል።

- እ.አ.አ የ2000 ዲሞግራፊና ጤና ጥናት (DHS) መረጃ Indicators በEthioInfo Database የማዘጋጀቱ ሥራ በከፊል ተጠናቋል።

- ኢ.ኤ.አ የ2004 የኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጥናቶች መረጃ Indicators በ Ethionfo Database የማዘጋጀቱ ሥራ በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡

## 7. ኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂን በተመለከተ

- መ/ቤቱ በሁለት የተለያዩ ግቢዎች ውስጥ የሚገኝ በመሆኑ በፋይበር ኦፕቲክስ ለማገናኘት የሚያስችል ሥራ ተከናውኖ በሁለቱም ግቢዎች ባሉ ባለሙያዎች መካከል የመረጃ ልውውጥና የኢንተርኔት አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

- በሁለቱ ግቢዎች መካከል ለተዘረጋው የኔትዎርክ መስመር አስፈላጊ የሆኑ መሣሪያዎች ግዥ እንዲሁም የኢንተርኔት አገልግሎቱ የተረጋጋ እንዲሆን የሚያስችል ሥራ ከኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን ጋር በመሆን ተከናውኗል፡፡

- የመ/ቤቱን የኔት ዎርክ ፖሊሲ በመቅረጽና በሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ጋር ተወያይቶ እንዲፀድቅና ተግባራዊ እንዲሆን የተደረገ ሲሆን፤ የኔት ወርክን አጠቃቀም በሚመለከት ለመ/ቤቱ ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

- የመ/ቤቱን መረጃዎች በ Electronic Format ለማዘጋጀት የሚያስችል የአራት ቀን ሥልጠና ለባለሙያዎች የተሰጠ ሲሆን፤ ከመምሪያዎች የተሰበሰበውንና የተዘጋጀውን አመታዊ መጽሔት ለመጀመሪያ ጊዜ በElectronic Format እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡

- የመ/ቤቱን ድህረ - ገጽ ለማዘጋጀት እንዲቻል የተለያዩ ሐገሮች የስታቲስቲክስ መ/ቤት ድረ - ገጽ በመጐብኘት የመ/ቤቱን web site Map የማዘጋጀት ሥራ ተጠናቆ፤ በመ/ቤቱ ሥራ አመራር እንዲፀድቅ ተደርጓል፡፡ ይህን ድህረ - ገጽ የመገንባቱን ሥራ ከCIDA በተገኘ የባለሙያዎች ድጋፍ አማካይነት ሥራው ተጠናቆ የሥራ አመራሩ አስተያየት እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡

- የመ/ቤቱን ሠራተኞች በ Personnel database ለመያዝ የሚረዳ ፕሮግራም ተዘጋጅቶና ተፈትሾ የመ/ቤቱ ሠራተኞች መረጃ ወደ ኮምፒውተር የማስገባቱ ሥራ የተጠናቀቀ ሲሆን ፤ የመረጃው

ትክክለኛነት በእያንዳንዱ ሠራተኛ እንዲታረምና እንዲረጋገጥ ለሚመለከተው ክፍል ተሰጥቷል፡፡

- መ/ቤቱ ለመረጃ ቅንብርና ትንተና የሚጠቀምባቸውን ኮምፒውተሮችና ተዛማጅ ዕቃዎችን አጠቃላይ ቆጠራ በማካሄድና database በማዘጋጀት ሪፖርቱ ለሚመለከተው አካል ቀርቧል፡፡

- የመ/ቤቱን የሂሳብና በጀት ዋና ክፍል ሥራ ቀልጣፋና የተሻለ ለማድረግ የሚያስችል አጠቃላይ እንቅስቃሴ እየተካሄደ ይገኛል፡፡ በመሆኑም ይህንን ሥራ ለማገዝ እንዲቻል በክፍሉ ያሉትን ኮምፒውተሮች እርስ በርስ እንዲገናኙ ተደርጓል፡፡

- የ68 ኮምፒውተሮችና የሁለት ፕሪንተሮችን ችግር መርምሮ በማየት 46 ኮምፒውተሮች በክፍሉ ባለሙያዎች እንዲጠገኑ የተደረገ ሲሆን፤ ቀሪዎቹ 22 ኮምፒውተሮችና ሁለት ፕሪንተሮች ለጥገና እንዲላኩ ተደርጓል፡፡

- የወረዳ ኔት ፕሮጀክት በተመለከተ በፌዴራል ደረጃ ከተቋቋመው ቴክኒካል ኮሚቴ ጋር በመሥራት መ/ቤቱን በሚመለከት አስፈላጊው ዶክመንት ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው ክፍል ተላልፏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ መ/ቤቱ የወረዳ ኔቱን በመጠቀም ሊሰበስበው ስለሚገባው መረጃ አስፈላጊው የዝግጅት ሥራ በመካሄድ ላይ ሲሆን፤ የወረዳ ኔቱን በመጠቀም ሊሰበስቡ የሚገባቸውን የመረጃ ዓይነቶች በመለየት ለዚሁ ተግባር የሚውሉ ፎርማቶች እንዲዘጋጁ ተደርጓል፡፡

- በማዕከል ደረጃ በተዘጋጀው የ1997 የኮንቴንትና አፕሊኬሽን ልማት ፕሮጀክት የሥራ መረሃ-ግብር የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ድርሻ እንዲካተት ተደርጓል፡፡

- መ/ቤቱ ባለፉት ዓመታት ሲያካሂዳቸው የነበሩ ጥናቶችን በተመለከተ ተበታትነው ያሉትን መረጃዎች በአንድ ማዕከላዊ ስፍራ (Centeral Data Bank) ለማከማቸት እንዲቻል ከአንድ አማካሪ ጋር በመሆን ለሥራው የሚሆን ዝግጅትና ዕቅድ ተዘጋጅቷል፡፡ በዚሁ መሰረት እስካሁን 68 የሚሆኑ ጥናቶችን ጥሬ መረጃና ተዛማጅ ዶኩመንቶች በማዕከል እንዲከማቹ ተደርጓል፡፡

- ለICT አቅም ግንባታ የተገዙ ዕቃዎችን ትክክለኛነት በማረጋገጥ ለመ/ቤቱ ሠራተኞች የሚሰጥበትን የድልድል ሥራ ተከናውኗል፡፡ እንዲሁም ለማዕከላዊ ዳታ ባንክ ግንባታ የሚያስፈልጉ የተጨማሪ ዕቃዎች ዝርዝር /specification/ ተዘጋጅቶ ለ UNDP ተልኳል፡፡

- ዘመናዊ የፕሮጀክት ማኔጅመንትን በተመለከተ ለመ/ቤቱ ባለሙያዎች ስልጠና ለመስጠት በታቀደው መሠረት ከኢንተርናሽናል ተቋም ጋር ግንኙነት በመፍጠር ለበላይ የሥራ አመራር አካላት ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

- የመ/ቤቱን ድረ - ገጽ ላይ አስፈላጊ ማሻሻያ ማድረግ ሲያስፈልግ መ/ቤቱ ባሉት ባለሙያዎች ማስተካከያውን ማድረግ እንዲችል ለአምስት ባለሙያዎች በ HTML ላይ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

- የመ/ቤቱን የውስጥ ለውስጥ ድረ - ገጽ /interanet/ ግንባታ በመካሄድ ላይ ሲሆን፤ ለመ/ቤቱ ባለሙያዎች ፍጆታ የሚሆኑ መረጃዎችን የያዘው ክፍል ተግባር ላይ ውሏል፡፡

- የመ/ቤቱ LOGO ሊሆኑ የሚችሉ አራት አማራጮች ተሠርተው እንዲቀርቡ ከተደረገ በኋላ የመ/ቤቱ የአመራር አካላት ለመ/ቤቱ የሚሆነውን እንዲመርጡ ተደርጐ የተመረጠው LOGO ተዘጋጅቷል፡፡

- በዳታ ኢንትሪ ክፍል ያስቸግር የነበረውን የኔትዎርክ መስመር በአዲስ መልክ የመዘርጋት ሥራ ተከናውኗል፡፡

- የICT የሥራ ድርሻና የሰው ሃይል አደረጃጀት በአዲስ መልክ ተዘጋጅቶ ቀርቧል፤

- እስካሁን ወደ ማዕከላዊ ሰርቨር የተሰበሰቡትን መረጃዎች ከጥሬ መረጃ በስተቀር ለኤሌክትሮኒክስ ስርጭት አመች ወደሆነው PDF ፎርማት የመቀየሩ ሥራ ተጠናቋል፡፡

- አጣዳፊ ሥራዎችንና መልዕክቶችን መለዋወጥ እንዲቻል ማዕካዊ ሰርቨሩን ማገናኘት የሚያስችል Remote Access Configure ተደርጎና ሙከራው ተካሄዶ በሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል።

- ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን የማገናኘቱን ሥራ ለመጀመር የሚያስችል የቅድመ ጥናት ለማካሄድ የሚያስችል ቢጋር ተዘጋጅቶ ለማኔጅመንት ለውሳኔ ቀርቧል።

- ለ ICT አቅም ግንባታ UNDP እንዲገዛላቸው የተጠየቁ ዕቃዎች ሲመጡ የሚያርፋበትን የቦታ ዝግጅትና ዕቃዎቹን Configure ለማድረግ ለሚወዳደሩ ድርጅቶች የማወዳደሪያ ቢጋር የማዘጋጀትና የተገዙት ዕቃዎች በተጠየቀው Specification መሠረት መሆናችን የማረጋገጥ ሥራ ተካሄዷል። እንዲሁም ከዋናው መ/ቤት ወደ ቅ/ጽ/ቤቶች የሚላኩ ኮምፒውተሮችን Configure የማድረግ ሥራ ተከናውኗል።

- የData Quality Check እና Dissemination Toolkit ሥልጠናውን ከሚሰጡት ባለሙያዎች ጋር አስፈላጊው የቅድመ ዝግጅት ሥራ የተጠናቀቀ ሲሆን፣ በመጪው መስከረም 1998 በአገር ውስጥ ለሚሰጡ የተለያዩ ICT ነክ ሥልጠናዎች የሥልጠና ተቋማትን ከወዲሁ የመለየት ሥራ ተሠርቷል።

## 8. የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ጽ/ቤት

### 8.1 የአሠራርና የአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻል ለማድረግ የተከናወኑ ሥራዎች

- በመ/ቤቱ የግብርና ስታቲስቲክስ መረጃ አቅርቦት እና በመረጃ ክምችትና ስርጭት ሁኔታዎች ላይ የአሠራርና የአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያ ጥናቶችን በማካሄድ መሰረታዊ ለውጥ ማምጣት በሚያስችሉ የአሰራርና የአገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት ለመተካት ሁለት ግብረ - ኃይሎች ተቋቁመው የማሻሻያ ጥናቶቹ በረቂቅ ደረጃ ተጠናቀዋል። በረቂቅ ደረጃ የተጠናቀቁት ጥናቶች በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ለሚመራው የበላይ አስተባባሪና ገምጋሚ ኮሚቴ ለውይይት ለማቅረብ ዶኩመንቱ ተሰራጭቷል።

- የማሻሻያ ጥናት ለሚካሄድባቸው ሁለት ጉዳዮች ቢጋሮች /TOR/ ተዘጋጅተው የየግብረ - ኃይሉ አባላት በሚመለከታቸው ቢጋር ላይ በዝርዝር ተነጋግረው ማሻሻያዎች አድርገው ተሠርቶባቸዋል፡፡

- የማሻሻያ ሥራዎችን የሚመራ የመምሪያና የአገልግሎት ኃላፊዎች እንደዚሁም የመ/ቤቱ የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ጽ/ቤት ኃላፊ አባል የሆኑበት የበላይ ሥራ አመራር ኮሚቴ ተቋቁሟል፡፡

- በሁለቱም ማሻሻያ ጥናቶች የተከናወኑ ከፊል ሥራዎች ላይ ቀደም ሲል በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ከፍተኛ ባለሥልጣናት በሚመራው የበላይ አስተባባሪና ግምገማ ኮሚቴ ታይተው የተሰጡት የማስተካከያ አስተያየቶች እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

- የግብርና ስታቲስቲክስ መረጃ አቅርቦት ማሻሻያ ጥናትን በተመለከተ በአሁኑ ጊዜ በአሠራር ላይ ያጋጠሙ ችግሮችና መንስኤዎቻቸውን የመተንተን እና ሊደረጉ የሚገባቸው የአሠራር ማሻሻዎች ተዘጋጅተው ለችግሮቹ መፍትሄ የመቀየስና ማሻሻያው የሚተገበርበት መርሃ ግብር በረቂቅ ደረጃ ተጠናቆ በመ/ቤቱ የበላይ ሥራ አመራር ኮሚቴ ውይይት ተደርጐበታል፡፡

- የመረጃ ክምችትና ስርጭትን በተመለከተም በጥናቱ መፈተሽና መታየት የሚገባቸው ታይተውና ተፈትሸው የማሻሻያ ጥናቱ ተጠናቆ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚመራው የበላይ አስተባባሪና ግምገማ ኮሚቴ የታየ ሲሆን የሚተገበርበት መርሃ-ግብር ተዘጋጅቶ ለመ/ቤቱ የበላይ ሥራ አመራር ቀርቧል፡፡

- በመ/ቤቱ አሠራርና በአገልግሎት አሠጣጥ ላይ መሠረታዊ ለውጥ ለማምጣት በሁለት የሥራ ዘርፎች ላይ የተጀመረው BPR ከጥር ወር 1997 ጀምሮ በሌሎች የሥራ ዘርፎችም በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡ በመሆኑም በመ/ቤቱ በሚገኙ የተለያዩ መምሪያዎችና እንደዚሁም አገልግሎቶች እስከ ሰኔ 30/1997 ድረስ ነባር አሠራሮችን የማስቀመጥ ሥራ የተጠናቀቁ ሲሆን ቀጣይ ሥራዎች እስከ ነሐሴ ወር መጨረሻ 1997 ድረስ ለማጠናቀቅ መረሃ - ግብር ተዘጋጅቷል፡፡

## 8.2 የQuick wins ሥራዎችን በተመለከተ የተከናወኑ ሥራዎች

- የመ/ቤቱን የፋይናንስ ዋና ክፍልና የኦዲት አገልግሎትን የሰው ሃይል፣ የቢሮ ዕቃዎችና ፋስሊቲዎች እንዲሁም የሥራ ግንኙነት ሁኔታን የሚዳስስ ጥናት ተካሄዶ ሪፖርቱ ተዘጋጅቷል፡፡

- የመ/ቤቱ የንብረት አስተዳደር ዘመናዊ አሰራርን የተከተለ እንዲሆን ለማድረግ፣ በተለያዩ ምክንያቶች መ/ቤቱን በለቀቁ ሠራተኞች ስም ተይዘው የሚገኙ የንብረት ሰነዶችና አገልግሎት ላይ ሊውሉ ያልቻሉ ዕቃዎች ላይ መፍትሄ መስጠት የሚያስችል ጥናት እየተካሄደ ይገኛል፡፡

- መ/ቤቱ የራሱ የሆነ ጋራዥ ለማቋቋም ያለው ሃሣብ መሠረት ያደረገ ጥናት በመካሄድ ላይ ሲሆን፤ ከአራት መንግሥታዊ ጋራዦች ልምድ ለማግኘት ተሰብስቧል፡፡

- የመሥሪያ ቤቱን ልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎች የሥራ ዝርዝር /ተግባርና ኃላፊነት የያዘ ጥራዝ ለማዘጋጀት በኮምፒውተር እየተጻፈ ነው፡፡

- ለቅ/ጽ/ቤቶች የሥራ መደቦች ስታቲስቲሽያን II እና III፣ ለዋናው መ/ቤት የእንግሊዝኛ ሰነጽሁፍ ኤክስፐርት VI፣ ነገረፈጅ መፕ VIII፣እና የሹፌር እፕ V የሥራ ዝርዝር ተዘጋጅቶ ለፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ቀርቦ የሥራ መደብ ቁጥር ተሰጥቷል፡፡

- የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች መኪናዎች በዋናው መ/ቤት በኩል ጋራዥ ለመግባት ርክክብና የሥራ ትዕዛዝ/ የጉዳት ማስታወቂያ ቅጽ ለማዘጋጀት የሚታለፈውን የአሠራር ሂደት በመፈተሽና በመገምገም የቀረበው የአሰራር ማሻሻያ የፖሊሲ አማካሪ ኮሚቴ አይቶት ትራንስፖርትና ጥገና ዋና ክፍል በሚያዘጋጀው BPR እንዲመለከተው ተሰጥቶታል፡፡

- በረቂቅ ደረጃ የተዘጋጀው የሥነ - ምግባርና ደንብ ላይ የመ/ቤቱ ዲስፕሊን ኮሚቴ አስተያየት እንዲሰጥበት ተሰጥቷል፡፡

- በግብርና ዘርፍ በሃገሪቱ በተለያዩ አካላት የሚቀርቡት መረጃዎች ከፍተኛ ልዩነት ያላቸው በመሆኑ ችግሩ እንዲፈታ በየደረጃው ውይይት ለማካሄድ የጋራ መግባባት የተደረሰበትን ለመተግበር የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ተካሂደዋል፡፡

## 9. የማስታወቂያና ሕዝብ ግንኙነት

- በ1997 ዓ.ም የዕቅድ ዘመን በመ/ቤቱ የተዘጋጁ 6,704 ልዩ ልዩ የጥናት ሪፖርቶች ለመንግሥት፣ ለዓለም አቀፍ ድርጅቶች፣ ለከፍተኛ የትምህርት ተቋማትና ለምርምር ማዕከሎች በነጻ ተሠራጭተዋል፡፡ በሌላ በኩል 2,914 ልዩ ልዩ የጥናት ሪፖርቶች በብር 84,844.45 ሽያጭ ተፈጽሟል፡፡ እንዲሁም ብር 120,840 የሚያወጡ የጥሬ መረጃዎች ለተለያዩ ድርጅቶችና ግለሰቦች ተሸጦ ለመንግሥት ገቢ ተደርጓል፡፡

- የመ/ቤቱ ልሳን የሆነው ልሳነ ማስባ ቅጽ 2 ቁጥር 3 እንዲሁም ልሳነ ማስባ ቅጽ 3 ቁጥር 4 መጽሔት ሁለቱም ተጠናቀው እያንዳንዳቸው 1500 ኮፒ የተሰራጨ ሲሆን፤ልሳነ ማስባ ቅጽ 4 ቁጥር 5 ዝግጅቱ ተጠናቆ ለህትመት ተዘጋጅቷል፡፡ የመ/ቤቱ የዜና መጽሔት /News Letter/ ዜና ማስባ ቅጽ 2 ቁጥር 1 እንዲሁም ቅጽ 2 ቁጥር 2 ሁለቱም ተጠናቀው እያንዳንዳቸው 1500 ኮፒ ተደርጐ ተሠራጭቷል፡፡

- የመ/ቤቱ የቴሌፎን ዳይሬክተሪ በአዲስ መልክ ተዘጋጅቶ ለሁሉም የሥራ ክፍሎች እና ቅ/ጽ/ቤቶች እንዲደርስ ተደርጓል፡፡

- የ1997 አዲስ ዓመት ምክንያት በማድረግ 6,000 የግድግዳና 2,500 የኪስ የቀን መቁጠሪያዎች ተዘጋጅተውና ታትመው ለሚመለከታቸው መሥሪያ ቤቶች እንዲሁም ለመ/ቤቱ ሠራተኞች ተሰጥቷል፡፡

- የመ/ቤቱን የ1996 ዕቅድ አፈጻጸምና የ1997 ዓ.ም የመ/ቤቱ የስታቲስቲክስ የሥራ ዕቅድ፣ የ1997 የሰብል ምርት ትንበያ ጥናት፣ የግብርና ናሙና ጥናት፣ የመ/ቤቱን የጥሬ መረጃ አሠጣጥ መመሪያ፣ በሀገሪቱ የቤት እንስሳት ላይ የተሰበሰበውን መረጃና በሁለተኛው

የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናትን ሁለተኛውን አገር አቀፍ የሰው ኃይል ጥናትና ስለኤች. አይ. ቪ / ኤድስ እና ሌሎች የአባለዘር በሽታዎችን በተመለከተ ስለሚያካሄደው ጥናት በሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ጋዜጣዊ መግለጫ ተሰጥቷል። በተጨማሪም በሬዲዮ በቴሌቪዥንና በጋዜጦች መ/ቤቱ ስለሚያካሂዳቸው ጥናቶችና የሥራ ኃላፊዎቹ የሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ሽፋን እንዲያገኝና ለህብረተሰቡ ግንዛቤ እንዲያስጨብጥ ተሞክሯል።

- የመ/ቤቱ ቤተ መጻህፍት ለመ/ቤቱ ሠራተኞችና ከውጭ ለሚመጡ ተገልጋዮች ያልተቋረጠ የንባብ፣ የመረጃ አቅርቦትና የትውስት አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል። እንዲሁም ከውጭ እና ከአገር ውስጥ ለቀረቡ የመረጃ ጥያቄዎች በወቅቱ ምላሽ እንዲያገኙ ተደርጓል።

- በ1997 በጀት ዓመት ውስጥ 40 አዳዲስ መፃህፍትን፣ 361 የመ/ቤቱን ሪፖርቶች፣ 174 የልዩ ልዩ ይዘት ያላቸው ጽሑፎችንና የሕትመት ውጤቶችን በመረከብና 139 የውጭ መጽሔቶችን በስጦታና በግዥ በማሰባሰብ ቤተመፃህፍቱን ይበልጥ ለማዳበር ጥረት ተደርጓል።

- ለመ/ቤቱ ሥራ አጋዥ የሚሆኑ መጻህፍትን እንዲገዙ የሥራ ክፍሎች በጠየቁት መሠረት የመጻህፍት ዝርዝር ለዕቃ ግዥ አካላት ተላልፏል።

- በቤተ መፃህፍቱ ውስጥ ለ187 የውጭ ተገልጋዮች የ2,970 ገጾች የፎቶ ኮፒ አገልግሎት በመስጠት ብር 742.50 ለመንግሥት ገቢ ተደርጓል:

- የመ/ቤቱን ዶክመንቴሽን ለማጠናከር የመ/ቤቱን ታሪካዊ ሂደት የሚያሳዩ መረጃዎች፣ በመ/ቤቱ የተካሄዱ ስብሰባዎችን፣ ሥልጠናዎችንና ማህበራዊ ነክ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ፎቶዎችና የቪዲዮ ምስሎችን እንዲሁም መ/ቤቱን በተመለከተ በተለያዩ ጊዜያት በመገናኛ ብዙሃን የተላለፉና በጋዜጦች ላይ የወጡ ጽሑፎችን ለመረጃነት በማሰባሰብ በሥርዓት እንዲቀመጡ ተደርጓል።

- የ1996 በጀት ዓመት የማስባ ዕቅድ አፈጻጸምን በሚመለከት በዓመታዊ የኢትዮጵያ መጽሐፍ እንዲወጣ ለማድረግ ተዘጋጅቶ ለማስታወቂያ ሚኒስቴር ተልኳል።

- መ/ቤቱ የሚያወጣቸው የጥናት ሪፖርቶች ጠቅለል ያለ መረጃ ለመስጠት የሚያስችል ብሮሽር በመዘጋጀት ላይ ይገኛል።

## 10. የኦዲት አገልግሎት

- በ1997 የዕቅድ ዘመን የ1996 ዓ.ም የንብረት ቆጠራና፣ የካርቶግራፊ የዕቃ ግምጃ ቤት ንብረት ምርመራ ተደርጎ ሪፖርት ለበላይ አካል ቀርቧል።

- በዋናው መ/ቤት የሚገኘው የመስክ ሥራ ክንውን መምሪያ የዕቃ ግምጃ ቤት የንብረት ቆጠራ ተጠናቆ የሰነድ ምርመራ እየተካሄደ ሲሆን፣ የመ/ቤቱ የመኪና ዕቃ መለዋወጫ ምርመራ ተካሄዶ ርክክቡ ለተተኪው ሠራተኛ ተፈጽሞ ሪፖርት ቀርቧል።

- የ1996 ዓ.ም የሂሳብ ምርመራ ተካሄዶ የተጠናቀቀ ሲሆን፣ የ1997 ዓ.ም ሂሣብ እስከ መጋቢት ወር ድረስ ያለው ምርመራ ተደርጓል። እንዲሁም የዋናው መ/ቤት ዋና ገንዘብ ያዥ የሣጥን ሂሣብ ምርመራ ተካሂዷል።

- የአሰበ ተፈሪ የስታቲስቲክስ ቅ/ጽ/ቤት ኃላፊ የሥራ ለውጥ በማድረጋቸው ያንቀሳቅሱት የነበረውን የመንግስት ገንዘብና ንብረት ምርመራ ተደርጎ ርክክብ የተፈፀመ ሲሆን፣ የቅ/ጽ/ቤቱም ዝርዝር የሂሳብ ምርመራም ተካሄዶ ሪፖርት ቀርቧል።

- ለሰራተኞች የሚሰጥ የረጂም ጊዜ የደመወዝ ብድር በየወሩ እየተቆረጠ ተመላሽ በሚደረገው ከሐምሌ 1996 እስከ ሚያዝያ 1997 ዓ.ም ምርመራ ተደርጓል።

## 11. ሕግ አገልግሎት

- ከመ/ቤቱ የዕቃ ግምጃ ቤት ሠራተኞች መካከል ሁለት ግለሰቦች በጠቅላላው ግምቱ ብር 75,688.98 የሚያወጣ ንብረት በማጉደላቸው እንዲከፍሉ ተጠይቀው አንደኛዋ ያጎደሉትን ብር 2,972.65 በተነገራቸው መሰረት ከደመወዛቸው አንድ ሶስተኛው እየተቀነሰ ገቢ እያደረጉ ሲሆን፣ በአንደኛው ግለሰብ ላይ በብር 72,716.33 እምነት የማጉደል ክስ ተመስርቶ ጉዳዩ በፍ/ቤት በቀጠሮ ላይ ይገኛል፡፡

- ከሰኔ 30/1996 ዓ.ም በፊት የተለያዩ ግለሰቦች የመ/ቤቱ ሠራተኞች በነበሩበት ወቅት ያጐደሉትን የመንግሥት ገንዘብ በተሰጣቸው ማስጠንቀቂያ መሠረት ከሐምሌ 1/1996 እስከ ሰኔ 30/1997 ድረስ በተደረገው ክትትል ብር 19,283 ለመ/ቤቱ ገቢ ሊሆን ችሏል፡፡

- መ/ቤቱ የጉዳት ካሳ እንዲከፍላቸው ሁለት ግለሰቦችና አንድ ድርጅት በተለያዩ ፍ/ቤቶች ያቀረቡት የብር 90,542.61 ክስ ክትትል እየተደረገባቸው ይገኛል፡፡ የመ/ቤቱ ሠራተኛ የነበሩ ግለሰብ ያጐደሉትን ብር 21,591.00 እና አንድ ግለሰብ የተማሩበትን የትምህርት ወጪ እንዲከፍሉ በብር 47,593.92 ላይ መ/ቤቱ ያቀረበው ክስ በፍ/ቤት ክትትል እየተደረገበት ይገኛል፡፡

- በሌላ በኩል መ/ቤቱ በጉዳት ካሳ እንዲከፍላቸው አንድ ግለሰብ ያቀረቡት የብር 116,000 ክስ በተደረገው ክትትል ፋይሉ ተዘግቶ መ/ቤቱ በነፃ ተሰናብቷል፡፡

- የቦሌ ማተሚያ ድርጅት በ1989 ዓ.ም መ/ቤቱ ጋር በገባው ውል መሰረት ሊከፍላቸው የሚገባውን ብር 708.75 እንዲከፈለው ህዳር 14/1997 በፍ/ቤት ክስ መስርቶ እስከ ዛሬ ክፍያውን ባለመጠየቁ ጥፋቱ የድርጅቱ በመሆኑ ወለድንና ሌሎች ወጪዎችን ሳይጨምር ዋናውን ገንዘብ መ/ቤቱ እንዲከፍል ፍ/ቤቱ ወስኗል፡፡

- እንደዚሁም መ/ቤቱ ያላግባብ ከሥራችን አባሮናል በማለት አራት ግለሰቦች በተለያዩ ፍ/ቤቶች መ/ቤቱ ላይ ያቀረቡት ክስ በተደረገው

ክትትል እርምጃው ትክክል እንደሆነ ፍ/ቤቱ አምኖበት ፋይሉ ተዘግቶ መ/ቤቱ በነፃ ተሰናብቷል፡፡

## 12. ፕላንና ፕሮግራም አገልግሎት

- በ1997 በጀት ዓመት መ/ቤቱ ለሚያካሂደዉ አንድ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከመንግሥት የተፈቀደዉን ካፒታል በጀት ከሚመለከታቸዉ መምሪያዎችና አገልግሎቶች ጋር በመሆን በወርሃዊ የሥራ መርሃ-ግብሩ መሠረት ወርሃዊ የገንዘብ ፍላጎት በማዘጋጀትና ለበላይ አካል በማቅረብ በሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡

- የመ/ቤቱን ወርሃዊ የፊዚካልና የፋይናንስ አጠቃቀም ሪፖርት በየወሩ እየተዘጋጀ ለሚመለከተዉ ክፍል እስተላልፏል፡፡

- የመ/ቤቱ የ1997 - 2001 (የአምስት ዓመት) የስትራቴጂክ ዕቅድና ሥራ አመራር ዶክመንት ከሚመለከታቸዉ የመምሪያና አገልግሎት ኃላፊዎች ጋር በመሆን ተዘጋጅቶና ተጠናቆ ለሚመለከታቸው ሁሉ እንዲደርስ ተደርጓል፡፡

- የ1997 በጀት ዓመት የመጀመሪያውን ሦስት ወራት፣ የስድስት ወራት እና የዘጠኝ ወራት ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው ክፍሎች እንዲደርስ ተደርጓል፡፡

- በመ/ቤቱ በ1998 የሚካሄዱ የሁለት ፕሮጀክቶችን የካፒታል በጀት ፍላጐትና የ1998 - 2000 (የሦስት ዓመት) የመንግሥት ኢንቨስትመንት ፕሮግራም በማዘጋጀት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር አቅርቧል፡፡

## 13. የአስተዳደርና ፋይናንስ አገልግሎት

### 13.1 የሰዉ ኃይል ሁኔታ

በ1997 በጀት ዓመት መጀመሪያ ላይ በባለሥልጣኑ መ/ቤት 1,535 ቋሚና 2,570 የኮንትራት በጠቅላላው 4,105 ሠራተኞች ነበሩ፡፡ በዕቅድ ዘመኑ ከሐምሌ 1/1996 እስከ ሰኔ 30/1997 ዓ.ም ድረስ ከቋሚ ሠራተኞች መካከል 44 ሠራተኞች በራሳቸው ፈቃድ መ/ቤቱን ሲለቁ 3 በዲስፕሊን ጉድለት

ከሥራ ተሰናብተዋል። እንዲሁም 15 በሞት ሲለዩ የ62 አዲስ ሠራተኞች ቅጥር የተፈጸመ ሲሆን 3 ሠራተኞች በመንግሥት ትዕዛዝ ወደ ስራ ተመልሰዋል። በሌላ በኩል በበጀት ዓመቱ 4,882 የኮንትራት ሠራተኞች ተቀጥረዋል። እነዚህም 4,601 ጀማሪ መረጃ ሰብሳቢዎች፣2 የጥበቃ ሠራተኛ፣ 36 ሹፌሮች፣ 4 የሂሳብ ሠራተኞች፣ 120 የዳታ ኢንትሪ ኦፐሬተሮች፣ 4 የኤዲቲንግ ኮዲንግ ሠራተኞች፣ 85 ጀማሪ ስታቲስቲሽያን፣27 የመስክ ሥራ ተቆጣጣሪዎችና 3 ፕሮግራመሮች ናቸው። በተመሣሣይ ወቅት በጠቅላላው 5,112 የኮንትራት ሠራተኞች ከሥራ የተሰናበቱ ሲሆን፤ በአሁኑ ሰዓት በመ/ቤቱ 2,339 የኮንትራት ሠራተኞች በሥራ ላይ ይገኛሉ።

በዚህም መሠረት በ1997 በጀት ዓመት መጨረሻ ላይ ያለው ጠቅላላ የሰው ኃይል 3,877 ሲሆን ከዚህ ውስጥ 1,538 ቋሚና 2,339 የኮንትራት ሠራተኞች ናቸው።

ሠንጠረዥ 2 የሰዉ ኃይል ሁኔታ

| ተ.ቁ | አጠቃላይ ሁኔታ | የሠራተኛ ቅጥር ሁኔታ | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ቋሚ | ኮንትራት | ድምር |
| 1 | በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ የነበሩ | 1,535 | 2,570 | 4,105 |
| 2 | አዲስ የተቀጠሩ | 62 | 4,883 | 4,944 |
| 3 | በመንግሥት ትዕዛዝ ወደ ሥራ የተመለሱ | 3 | - | 3 |
| 4 | ሥራ የለቀቁ | (47) | (5,112) | (5,259) |
| 5 | በሞት የተለዩ | (15) | - | (15) |
| 6 | አሁን በሥራ ላይ ያሉ | 1,538 | 2,339 | 3,877 |

የቋሚ ሠራተኞች ሁኔታ በአገልግሎት ዓይነት ሲተነተን ፕሮፌሽናል 142 ፣ መለስተኛ ፕሮፌሽናል 826፣ ሲሆኑ 570 የአስተዳደር የጽህፈትና የጠቅላላ አገልግሎት ሠራተኞች ናቸው።

በ1997 የዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ ላይ ያሉት የመ/ቤቱ ቋሚና የኮንትራት ሠራተኞችን ሁኔታ በሥራ መደብ በመለየት በሚከተለው ሠንጠረዥ ለማቅረብ ተሞክሯል።

የሠራተኞች ሁኔታ በሥራ መደብ

ሠንጠረዥ 3

| ፆታ | ቋሚ | | | | ኮንትራት | | | | ጠቅላላ ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ፕሮፌሽናል | መለስተኛ ፕሮፌሽናል | ድጋፍ ሰጪ | ድምር | ፕሮፌሽናል | መለስተኛ ፕሮፌሽናል | ድጋፍ ሰጪ | ድምር | |
| ወንድ | 123 | 731 | 342 | 1,196 | 47 | 1,658 | 121 | 1,826 | 3,022 |
| ሴት | 19 | 95 | 228 | 342 | 2 | 336 | 175 | 513 | 855 |
| ድምር | 142 | 826 | 579 | 1,538 | 49 | 1,994 | 296 | 2,339 | 3877 |

## 13.2 <u>የበጀት አጠቃቀም</u>

ለ1997 በጀት ለባለሥልጣኑ መ/ቤት ከመንግሥት የተፈቀደለት የካፒታልና የመደበኛ በጀት በጠቅላላው ብር 47,513,100 ነው። ከዚህ ውስጥ ብር 32,871,200 ለብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም የሚውል የካፒታል በጀት ሲሆን፣ ብር 14,641,900 ለመደበኛ ሥራ ማስኬጃና ለደመወዝ የሚውል ነው።

### ሀ. የመደበኛ በጀት አጠቃቀም

በበጀት ዓመቱ ከተመደበው የመደበኛ በጀት ብር 14,641,900 ውስጥ ብር 13,314,200 ለሠራተኛ ደመወዝ የሚከፈል ሲሆን፣ ብር 1,327,700 ለሥራ ማስኬጃ የሚውል ነው።

በዚሁ መሠረት ለበጀት ዓመቱ ከተመደበው ብር 14,641,900 ውስጥ ከሐምሌ 1/1996 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30/1997 ድረስ ብር 14,641,900 ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ተጠይቆ ገቢ ሆኖ ብር 14,621,774.50 ሥራ ላይ ውሏል። ሥራ ላይ ከዋለው ውስጥ ብር 13,313,580.50 (91%) ለደመወዝ የተከፈለ ሲሆን፣ ብር 1,308,191.52 (8.94%) ደግሞ ለሥራ ማስኬጃ የዋለ ነው። በጠቅላላው ሥራ ላይ የዋለው ገንዘብ ለበጀት ዓመቱ ከተመደበው ጋር ሲነፃፀር 99.86 ከመቶ እንደሆነ ያመለክታል።

የመደበኛ በጀት አጠቃቀም

ሠንጠረዥ 4

| የወጪ ርዕስ | ለዓመቱ የተመደበ በጀት | በበጀት ዓመቱ ከተፈቀደዉ ዉስጥ ተጠይቆ የመጣ | ተጠይቆ ገቢ ከሆነዉ ዉስጥ ሥራ ላይ የዋለ | የአፈፃፀም በመቶኛ | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | በዓመቱ በእጂ ከገባው | በዓመቱ ከተፈቀደው |
| 01 | 02 | 03 | 04 | 05 | 06 |
| ደመወዝ | 13,314,200 | 13,314,200 | 13,313,581 | 99.99 | 99.99 |
| ሥራ ማስኬጃ | 1,327,700 | 1,327,700 | 1,308,194 | 98.5 | 98.5 |
| ድምር | 14,641,900 | 14,641,900 | 14,621,775 | 99.86 | 99.86 |

ለ. <u>የካፒታል በጀት አጠቃቀም</u>

የባለሥልጣኑ መ/ቤት በ1997 የዕቅድ ዘመን ለሚያካሂደው የብሔራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፕሮግራም ብር 32,871,200 የካፒታል በጀት ከመንግስት ተፈቅዷል።

በዚሁ መሠረት ከሐምሌ 1 ቀን 1996 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30 ቀን 1997 ድረስ ብር 32,871,201 ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ተጠይቆ ገቢ የተደረገ ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥ ብር 26,254,631.86 ሥራ ላይ ውሏል። ሥራ ላይ የዋለው ገንዘብ ለበጀት ዓመቱ ከተፈቀደው ጋር ሲነፃፀር 79.80 ከመቶ ሲሆን፤ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ተጠይቆ በእጅ ከገባው ጋር ሲነፃፀር ደግሞ በተመሳሳይ 79.80% እንደሆነ ያመለክታል። ዝርዝሩ በሠንጠረዥ አምስት ላይ የቀረበ ሲሆን፤ በበጀት ዓመቱ የበጀት እጥረት ያለባቸው ንዑስ የሂሣብ መደቦች ላይ የበጀት ዝውውር ተጠይቆ ጉድለቱ እንዲስተካከል ተደርጓል።

## የ1997 በጀት ዓመት

## የካፒታል በጀት አጠቃቀም

ሠንጠረዥ 5

| የሂሣብ መደብ | ለ1997 በጀት ዓመት ከመንግሥት ግምጃ ቤት የተፈቀደና የተስተካከለ በጀት | የተስተካከለ በጀት | በበጀት ዓመቱ ከተፈቀደው ከገንዘብ ሚ/ር ተጠይቆ በእጅ የገባ | ተጠይቆ በእጅ ከገባው በበጀት ዓመቱ ሥራ ላይ የዋለው | ሥራ ላይ የዋለው ገቢ ከተደረገው አፈጻጸም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 |
| 6113 | 14,148,000 | 13,209,355 | 13,209,355 | 9,984,555 | 75.6 |
| 6114 | 1,033,000 | 1,033,000 | 1,033,000 | 1,023,808 | 99.4 |
| 6123 | 379,000 | 670,620 | 670,620 | 643,551 | 95.9 |
| 6212 | 200,000 | 200,000 | 200,000 | 152,034 | 76.0 |
| 6213 | 336,000 | 336,000 | 336,000 | 122,688 | 36.5 |
| 6217 | 2,010,700 | 2,010,700 | 2,010,700 | 1,661,930 | 82.6 |
| 6231 | 11,369,000 | 11,369,000 | 11,369,000 | 8,521,404 | 74.9 |
| 6232 | 433,000 | 483,000 | 483,000 | 573,902 | 118.8 |
| 6241 | 1,240,000 | 1,445,000 | 1,445,000 | 1,525,704 | 105.6 |
| 6243 | 45,000 | 45,000 | 45,000 | - | - |
| 6252 | 263,000 | 489,628 | 489,628 | 478,249 | 97.7 |
| 6254 | 939,500 | 1,061,500 | 1,061,500 | 1,065,775 | 100.4 |
| 6257 | 37,000 | 55,750 | 55,750 | 53,343 | 95.7 |
| 6258 | 336,000 | 336,000 | 336,000 | 295,663 | 87.9 |
| 6259 | 52,000 | 74,500 | 74,500 | 98,725 | 132.5 |
| 6271 | 50,000 | 52,167 | 52,167 | 27,448 | 52.6 |
| ድምር | **32,871,200** | **32,871,200** | **32,871,200** | **26,228,779** | **79.8** |

### 13.3 አገልግሎት ነክ የሆኑ ሥራዎች

#### 13.3.1 ጠቅላላ አገልግሎት ዋና ክፍል

- ለ1997 በጀት ዓመት በዋናው መ/ቤትና የስታቲስቲክስ ቅ/ጽ/ቤቶች የደንብ ልብስ የሚያስፈልጋቸውን የሠራተኛ ቁጥር በማጣራትና መረጃውን በማሰባሰብ ጨረታ በጋዜጣ እንዲወጣ በማድረግ የጨረታ አሸናፊው ተለይቶ የተመረጠው ልብስ ገቢ የተደረገ ሲሆን፣ በክፊል

የልብስ ስፌት ሥራው ተጠናቆ በሚመለከታቸው ሠራተኞች ተጠቃሚ ሆነዋል። የአላቂ ዕቃዎችን በሚመለከት ማስታወቂያው በጋዜጣ ወጥቶ አሸናፊው ተለይቶ በአብዛኛው ግዥው የተፈፀሞ ስሥራ እንዲበቁ ተደርገዋል።

- በአዲስ አበባ ስታቲስቲክስ ቅ/ጽ/ቤት ቀደም ሲል ለተጀመረው የአጥር ሥራ የመጨረሻው የቆርቆሮ ማልበስ ሥራ ተጠናቋል። እንዲሁም ከቴሌኮሙኒኬሽን መ/ቤት ጋር በመነጋገር ብልሽት የደረሰባቸው ስልኮች እንዲሠሩ ጥረት ተደርጓል።

- ከየቅ/ጽ/ቤቶች ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ሪፖርት በማሰባሰብ ለመረጃነት በሥርዓት እንዲቀመጡ ተደርጓል።

- ከሐምሌ 1/1995 እስከ ሰኔ 30/1996 ድረስ ከዋናው መ/ቤት ለየቅ/ጽ/ቤቶቹ የተላኩ የተለያዩ ንብረቶች በትክክል ስለመድረሳቸው የየቅ/ጽ/ቤቶች ኃላፊዎች በዕቃ ዝርዝሮቹ መሠረት ማረጋገጫ እንዲያቀርቡ በተጠየቀው መሰረት ተገቢው ምላሽ ተገኝቷል።

- በመ/ቤቱ ከአገልግሎት ውጭ የሆኑ አሮጌ ወንበርና ጠረጴዛዎችን፣ አሮጌ ከረጢቶች በጨረታ አወዳድሮ ለመሸጥ በታቀደው መሠረት ጨረታው ተካሂዶ አሸናፊውን በመለየት በጨረታ ተሸጠው እንዲወገዱ ተደርጓል።

- የቅ/ጽ/ቤቶችን የንብረት አያያዝ፣ አጠቃቀምና የአሠራር ሂደታቸውን በመገምገም ሙያዊ ዕገዛ ለማድረግ በታቀደው መሠረት በሁለት ዙር የመስክ ጉብኝት 15 ቅ/ጽ/ቤቶችን በመመልከት አጠቃላይ ሪፖርት ለበላይ አካል ቀርቧል።

- በ1996 ዓ.ም በጀት ዓመት ግዥ የተፈጸመባቸውን ንብረቶች መረጃዎችን በማጣራት የንብረቶቹ ዝርዝር ተለቅሞ መረጃው የተዘጋጀ ሲሆን፣ ከተለያዩ የሥራ ክፍሎች በቀረበው የግዥ መጠየቂያ መሠረት የኮምፒውተር ቶነሮች፣ የተለያዩ የህትመት ዕቃዎችና ሌሎች የተለያዩ ዕቃዎች ግዥ ተፈጽሟል።

- መ/ቤቱ የተጠቀመባቸው የስልክ፣ የመብራትና የውሃ ፍጆታ የክፍያ ጥያቄ ቢሉን በማየት አስፈላጊውን መረጃ በመያዝ ለክፍያ እንዲቀርብ ተደርጓል።

- በመ/ቤቱ ከአገልግሎት ውጪ የነበሩ ተሽከርካሪዎችን እንዲወገዱ በተወሰነው መሠረት በግልጽ ጨረታ ወጥቶና ሺያጩ ተፈጽሞ ገንዘቡ ለመንግሥት ገቢ ሆኗል።

- ከውጪ በዕርዳታ የመጡ ኮምፒውተሮች ከጉምሩክ ወደ መ/ቤቱ እንዲገቡ ተደርጐ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል።

- ለመ/ቤቱ አገልግሎት ይሰጡ በነበሩ ብልሽት የደረሰባቸው የተለያዩ ፎቶ ኮፒ ማሽኖች፣ ኮምፒውተሮች፣ ፕሪንተሮችና የህትመት ማሽኖች ወዘተ የመሳሰሉት ተጠግነው ለአገልግሎት እንዲበቁ ሆነዋል።

- የመ/ቤቱን የቆርቆሮ መጋዘን፣ አጥርና የመፀዳጃ ቤቶች ጠቅላላ ዕድሳት በማድረግ የተሟላ አገልግሎት እንዲሰጡ ተደርጓል።

- የዕቃ ግዥ መመሪያ ቁጥር 1/1991 የንብረት መመሪያ ቁጥር 6/1991 ለስታቲስቲክ ቅ/ጽ/ቤቶች እንዲደርሳቸው ተደርጓል።

- ለመ/ቤቱ ለተለያዩ ሥራዎች አገልግሎት የሚውሉ ቋሚ ዕቃዎች ለዋናው መ/ቤትና ለቅ/ጽ/ቤቶች በተገቢው መንገድ በማከፋፈል አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ።

13.3.2 ትራንስፖርትና ጥገና ክፍል

- በበጀት ዓመቱ በባለሥልጣኑ መ/ቤት የሚገኙ ከ200 በላይ የመስክና የሰርቪስ ተሽከርካሪዎች በደንበኞችና በመ/ቤቱ ጋራዥ ተጠግነው ለሥምሪት ብቁ የተደረጉ ሲሆን፣ ከነዚህ ውስጥ 70 ተሽከርካሪዎች በዋናው መ/ቤት ጋራዥ ጥገና የተደረገላቸው ናቸው። እንዲሁም የዋናው መ/ቤት መካኒኮች ወደቅ/ጽ/ቤቶች በመንቀሳቀስ 9 የቆሙ ተሽከርካሪዎችን በመጠገን ወደ ሥራ እንዲሠማሩ ተደርጓል።

- አደጋ ለደረሰባቸው የመ/ቤቱ 42 ተሽከርካሪዎች በኢንሹራንስ ተሠርተው ወደ ምድብ ቦታቸው የተሰማሩ ሲሆን፣ 4 ተሽከርካሪዎች በኢንሹራንስ ጋራዥ በጥገና ላይ ይገኛሉ። ሁሉም የመ/ቤቱ ተሽከርካሪዎች ዓመታዊ ደህንነት ምርመራ ተደርጐላቸው ቴክኒካዊ ብቃታቸው ተረጋግጦ የብቃት ማረጋገጫ መረጃ እንዲያገኙ ተደርጓል።

- 210 ተሽከርካሪዎች የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በገባው ውል መሠረት የመድን ሽፋን እንዲያገኙ ተደርጓል።

### 13.3.3 ሕትመት ዋና ክፍል

በበጀት ዓመቱ ውስጥ በጠቅላላው 351,214 ጥራዝ ጠቅላላ የገጽ ብዛታቸው 11,092,642 የሆኑ የሕትመት ሥራዎች ለመ/ቤቱ የተለያዩ የሥራ ክፍሎች አገልግሎት ሰጥቷል።

## 14. ኤች.አይ.ቪ. /ኤድስን በተመለከተ

- በበጀት ዓመቱ ውስጥ ባለፉት ተከታታይ ዓመታት እንደተደረገው ሠራተኛው በፈቃደኝነት በወሰነው መሠረት በየወሩ ከሚያገኘው ደመወዝ ላይ የተወሰነ ገንዘብ እየተቆረጠ ለተስፋ ጐህ ማህበር ገቢ ተደርጓል።

- መ/ቤቱ በየሩብ ዓመቱና በየስድስት ወሩ በሚያወጣው ዜና መጽሔትና ልሣነ ማሰባ ላይ ቀስቃሽና ትምህርት ሰጪ የሆኑ ጽሑፎች እንዲወጡ የተደረገ ሲሆን፤ የኤች.አይ.ቪ. /ኤድስን በተመለከተ የሚያገኛቸውን ፖስተሮችና በራሪ ጽሑፎች ሠራተኛው ሊያገኛቸው በሚችልበት ቦታ ላይ በማስቀመጥ ግንዛቤ እንዲያገኙ አድርጓል።

- አብዛኛው የቅ/ጽ/ቤት ሠራተኞች ለስልጠና ወደዋናው መ/ቤት የሚመጡበትን ጊዜ በመጠበቅና ፕሮግራም በመያዝ ትምህርት ሰጪ የሆነ ድራማ እንዲመለከቱ በማድረግ የችግሩን ስፋት ሠራተኞች እንዲገነዘቡ አድርጓል። በተጨማሪም በሴቶች ላይ የሚደርሰውን የባህል ተፅዕኖ በሚመለከት ለዋናው መ/ቤት ሠራተኞች «ዶሮ ዳባ» የሚል ድራማ እንዲመለከቱ ተደርጓል።

## 15. በዕቅድ አፈፃፀሙ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች

- የአገሪቱን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ገጽታዎች የሚያመለክቱ ስታቲስቲካዊ መረጃዎች ሰብስቦና አጠናቅሮ ለመረጃ ተጠቃሚዎች በወቅቱ የማቅረቡ ተግባር የባለሥልጣኑ መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡ ይህንን መወጣት ይቻል ዘንድ በየዘርፉ የሰለጠነና ልምድ ያካበተ ባለሙያ መኖር ያስፈልጋል፡፡ የስታቲስቲክስ ሥራ ብቃት ያላቸውን የቴክኒክ ሰዎችን በተለይም ብቃት ያለው የሜቶዶሎጂ፣ የመረጃ ቅንብር ሥራዎችና ጥልቅ ትንተናና ምርምር የሚሰሩ ባለሙያዎችን ማሰማራትን ይጠይቃል፡፡ ካለበለዚያ በውጪ አማካሪዎች /ኮንሰልታንቶች/ ላይ ጥገኛ መሆንን ያስከትላል ስለሆነም ባለስልጣን መ/ቤቱ ብቃት ያላቸው በሳል ባለሙያዎችን እንዲይዝ የተሻለ የደመወዝ ስኬል መ/ቤቱ እንዲኖረው ማድረግን ይጠይቃል፡፡ ይህ ባለመሆኑ በበጀት ዓመቱ ከመ/ቤቱ በርካታ ፕሮፌሽናሎች ሥራቸውን ለቀዋል፡፡

- እያደገ የመጣውን የመረጃ ፍላጐት ለማሟላት እንዲቻል በየወቅቱ ቁጥራቸው በዛ ያለ ባለሙያዎች የሚቀጠሩ ሲሆን፣ ከዚህ በፊትም የተቀጠሩት ለሥራቸው ምቹ የሆነ ቢሮ ለማግኘት ከመ/ቤቱ አቅም በላይ እየሆነ መጥቷል፡፡ ይህም በመሆኑ በርካታ የሥራ ኃላፊዎችና ኤክስፐርቶቻቸው ተራርቀው የሚሰሩበት እንዲሁም አንድ ክፍል ከአቅም በላይ የሆነ የሰው ብዛት እንዲይዝ በማድረጋችን ቢሮዎቻችን ለሠራተኞች የተመቹ የሥራ ቦታ ሊሆኑ ባለመቻላቸው የሠራተኞች የሥራ ተነሣሽነት እየቀነሰ የሚመጣበት ሁኔታን እየፈጠረ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም ከፍተኛ የመንግስት ሃብት የወጣባቸው የተለያዩ የመስክ መገልገያ ዕቃዎች፣ በተለያዩ ጊዜያት መረጃ የተሰበሰበባቸው የጥናት ዶኩመንቶችና ሌሎች ቁሣቁሶች አመች የሆነ ማከማቻ መጋዘን ባለማግኘታቸው ችግሩን የተደራረበ አድርጐታል፡፡ እንዲሁም በመላው አገሪቱ የተከፈቱ የስታቲስቲክስ ቅ/ጽ/ቤቶች ላይ ተመሣሣይ የሆነ የቢሮና የመጋዘን ችግር ያላባቸው ሲሆን፣ በዓመት መንግሥት ለዋና መ/ቤትና ለቅ/ጽ/ቤቶቹ ከግማሽ ሚሊዮን ብር በላይ ለኪራይ ወጪ ያደርጋል በመሆኑም ለዋናው መ/ቤትና ለቅ/ጽ/ቤቶቻችን ለሥራ አመቺ የሆነ ቢሮ ለማግኘት እንድንችል ህንጻዎች የሚገነቡበት ሁኔታ መመቻቸት ይኖርበታል፡፡